# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 081 ኅዳር 21 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









## 28ኛው የአየር ንብረት ለውጥ

### ጉባዔ በዱባይ እየተካሄደ ነው

-የኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራ መካነ ርዕይ ለተሞክሮ ቀርቧል


ገጽ 4







## በመዲናዋ

### በቅርቡ ከፍተኛ የምርት አቅርቦት ይኖራል


ገጽ 4




አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ

## ኢትዮጵያ ብሪክስን

### የተቀላቀለችው ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስጠበቅ ነው

ተስፋ ፈሩ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ብሪክስን የተቀላቀለችው ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስጠበቅ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ ገለፁ፡፡

የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል ከመሆኗ ጋር በተያያዘ ያሉ ብዥታዎችን ለማጥራት እና በዓለም አቀፍ ደረጃ


ኢትዮጵያ ብሪክስን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት

### የማሻሻያ አዋጅ በሙሉ ድምጽ ጸደቀ

-አዋጁ በልዩ ልዩ አማራጮች የይዘት ተደራሽነትን ለማስፋት ያስችላል

ዘሳለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጀመራቸውን የሪፎርም ሥራዎች ለማጠናከር፣ የይዘት ሥራዎችን ተደራሽነት ለማስፋት እና የመንግሥት የፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር መርሆዎችን የተከተለ አሠራር ለመዘርጋት የሚያስችለው አዋጅ ጸደቀ። አዋጁ፤ ድርጅቱ በልዩ ልዩ አማራጮች የይዘት ተደራሽነቱን እዲያሰፋ የሚያደርግ መሆኑም ተገልጿል፡፡

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 7ኛ መደበኛ ጉባዔ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያን መርምሮ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል። አዋጁ ለተቋሙ በህትመት ተደራሽነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪነት በልዩ ልዩ የይዘት ማስተላለፊያ አማራጮች እንዲሰማራ የሚፈቅድለት ነው።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ የተከበሩ አቶ ታገሰ ጫፎ፤ ድርጅቱ እስካሁን ያለውን አቅም


የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የማሻሻያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




የተከበሩ አቶ ታገሰ ጫፎ፤







# የኢትዮጵያን መጻኢ ዕድል ለሚወስኑ ተማሪዎች ስለሀገራቸው ይበልጥ ማስገንዘብ ይገባል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን መጻኢ ዕድል ለሚወስኑ የዛሬ ዘመን ተማሪዎች ስለሀገራቸውና መወጣት ስላለባቸው ሃላፊነት ይበልጥ ማስገንዘብ ይገባል ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ ሃላፊ ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ለ18ኛ ጊዜ የሚከበረውን የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ምክንያት በማድረግ በአዲስ አበባ ከተማ ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች በተውጣጡ ተማሪዎች መካከል የጥያቄና መልስ ውድድር ትናንትና ተካሂዷል።

የቢሮው ሃላፊ ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያ ቀጣይ እጣ ፈንታ የሚወሰነው በትውልዱ በተለይም ዛሬ ላይ ባሉ ተማሪዎች ነው።

በመሆኑም ተማሪዎች ስለሀገራቸው ሁለንተናዊ ሁኔታና በቀጣይ ስለሚጠብቃቸው ሃላፊነት በአግባቡ ማስገንዘብ ይገባል ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ ዶክተር ዘላለም ገለጻ፤ የጥያቄና መልስ መርሀ-ግብሩ ተማሪዎች እርስ በእርስ ከመተዋወቅ ባለፈ ስለ ዴሞክራሲያዊና ሕገመንግሥታዊ ሥርዓት በመገንዘብ በጋራ ለሀገራቸው መቆም እንዲችሉ ግንዛቤ የሚፈጥር ነው።

ውድድሩ ተማሪዎች ከሕገመንግሥትም ሆነ የፌዴራል ሥርዓት ጋር በተገናኘ ያላቸው ግንዛቤ ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ የሚያስችል መሆኑንም አስገንዝበዋል።

ተማሪዎች በሕገመንግሥታዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ዕውቀት ለማሳደግ የሚረዱ ውድድሮች በቀጣይ ማካሄድ እንደሚገባም አሳስበዋል።

የጥያቄና መልስ ውድድሩ ከትምህርት ቤት ጀምሮ እስከ ከተማ መስተዳድር ድረስ በስኬት እንዲካሄድ አስተዋጽኦ ላበረከቱ የትምህርት አመራሮች፣ ባለሙያዎችና መምህራን ምስጋና አቅርበዋል።



በውድድሩ አሸናፊ የሆኑ ተማሪዎች ሽልማት ተበርክቶላቸዋል

በማጠቃለያ ውድድሩ ላይ ቀደም ሲል ከትምህርት ቤት ጀምሮ እስከ ክፍለ ከተማ ድረስ ሕገመንግሥታዊና የፌዴራሊዝም ሥርዓትን መሠረት ባደረጉ ጥያቄዎች በተካሄደው ውድድር በአማርኛና በአፋን ኦሮሞ ቋንቋዎች አሸናፊ የሆኑ 10 ተማሪዎች ተሳትፈዋል፡፡

በአማርኛ ዘርፍ ውድድሩን በበላይነት ያጠናቀቀችው ተማሪ ሱመያ አልዩ፤ የፍጻሜውን ጨምሮ ከትምህርት ቤት ጀምሮ ሲካሄድ በቆየው በዚህ ውድድር አማካኝነት ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ፣ ሕገመንግሥታዊና የፌዴራሊዝም ሥርዓት ያላትን እውቀት ማዳበር እንደቻለች በመግለጽ ውድድሩ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ተናግራለች፡፡

በአፋን ኦሮሞ ዘርፍ ውድድሩን በበላይነት ያጠናቀቀው ተማሪ አብዲ ታምሩ በበኩሉ፤ ውድድሩን በአሸናፊነት በማጠናቀቁ ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማውና ያገኘው የታብሌት ሽልማትም በቀጣይ በትምህርቱ ላይ ጠንክሮ በመሥራት የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግብ አቅም እንደሚሆንለት ጠቁሟል።

የውድድሩ አሸናፊዎች ታብሌት፣ የተለያዩ መጽሐፍት እዲሁም የሰርተፍኬት ሽልማቶች ተበርክቶላቸዋል።

# የአካል ጉዳተኝነት አካታችነትን ከዘላቂ ልማት ስትራቴጂዎች ጋር ማስተሳሰር ያስፈልጋል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የአካል ጉዳተኝነት አካታችነትን አግባብነት ካላቸው የዘላቂ ልማት ስትራቴጂዎች ጋር ማስተሳሰር ያስፈልጋል ሲሉ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር) ተናገሩ።

ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ቀን "ለአካል ጉዳተኞች ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ስኬት ትርጉም ያለው ትብብር" በሚል መሪ ቃል ህዳር 23 ቀን 2016 ዓ.ም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት በአሶሳ ከተማ ይከበራል። ሚኒስትሯ ይህን በሚመለከት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ የአካል ጉዳተኞች መብቶች በችሮታ የሚሰጣቸው ሳይሆን ሕገመንግሥታዊ መብታቸው ነው።

የአካል ጉዳተኝነት አካታችነትን አግባብነት ካላቸው የዘላቂ ልማት ስትራቴጂዎች ጋር ማስተሳሰር ስለማስፈለጉ የጠቀሱት ሚኒስትሯ፤ ይህም በማንም ይሁንታ የሚሰጣቸው ሳይሆን ሕገመንግሥታዊ መሆኑን ተናግረዋል።

በመሠረታዊነት የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ ለአንድ ተቋም ወይም ለመንግሥት ብቻ የሚተው ጉዳይ አለመሆኑን የገለጹት ሚኒስትሯ፤ የሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የጋራ ርብርብ የሚጠይቅ ትልቅ ኃላፊነት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት ተቀብላ ያጸደቀች እንደመሆኗ መንግሥት ከሕገመንግሥቱ ጀምሮ ለአካል ጉዳተኞች መብት መከበር በርካታ ሕጋዊና



ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር)

አስተዳደራዊ ርምጃዎችን ሲወስድ ቆይቷል ያሉት ሚኒስትሯ አሁንም ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

ሚኒስትሯ በዓለም ለ32ኛ ጊዜ በሀገር አቀፍ ደረጃ ደግሞ ለ31ኛ ጊዜ የሚከበረው የአካል ጉዳተኞች ቀን የህብረተሰቡን ግንዛቤና ምላሽ ሰጪነት በሚያሳድጉ ልዩ ልዩ መርሀ ግብሮች በአሶሳ ይከበራልም ብለዋል።

የዝግጅቱ ዋና ዓላማ የሕዝብ ንቅናቄ በመፍጠር አካል ጉዳተኞች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ እኩል እድል በመስጠትና ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸውን በማረጋገጥ ረገድ እንደሀገር ለሚደረገው ርብርብ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ለማሳሰብ ስለመሆኑም ሚኒስትሯ አብራርተዋል።

የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን ከተሠመረተባቸው መርሆዎች መካከል በግል ምርጫ የመወሰን ነጻነት፣ ራስን ችሎ የመኖር መብት ለተፈጥሯዊ ክብርና ለግለሰባዊ ልዕልና ክብር መስጠት፣ ከመገለልና መድልዎ ነጻ መሆን፤ የተሟላና ውጤታማ ተሳትፎና ማህበረሰባዊ አካታችነት፣ ለልዩነቶች ዋጋ መስጠት የሚሉት በዋነኝነት ይገኙበታል። በተያያዘም ዘንድሮ ለ16ኛ ጊዜ የተከበረው የአፍሪካ ወጣቶች ወር የማጠቃለያ መርሐ ግብር "ድንበር ተሻጋሪ የወጣቶች እንቅስቃሴ ለፓን-አፍሪካኒዝም" በሚል መሪ ቃል ተካሂዷል።

በመድረኩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት ሚኒስትሯ እንደገለፁት፤ በዚህ የግሎባላይዜሽን እና የመተሳሰር ዘመን በወጣቶቻችን መካከል የፓን አፍሪካዊ ማንነት ስሜት እንዲኖረን ማድረግ ወሳኝ መሆኑን ገልፀዋል።

# አስተዳደሩ የሥራ እድል ፈጠራ ላይ እንዲያተኩር ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

**-በዘርፉ በሩብ ዓመቱ 15 ሺህ 381 የሥራ እድል ተፈጥሯል**

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እና ይዞታ አስተዳደር በሥራ እድል ፈጠራ ላይ ትኩረት አድርጎ ሊሠራ እንደሚገባ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ፡፡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤ የአስተዳደሩን የ2016 ዓ.ም የአንደኛ ሩብ ዓመት አፈጻጸም ገምግሟል፡፡

የቋሚ ኮሚቴው ዋና ሰብሳቢ ፕሮፌሰር መሀመድ አብዶ በቀረበው ሪፖርት ላይ ምላሽ በሰጡበት ወቅት እንደገለጹት፤ የሥራ እድል ፈጠራው በቀረበበት ወቅት ከተፈጠረው የሥራ እድል ለምን ያህል ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል እንደተፈጠረ ሪፖርት አልቀረበም፡፡

በመሆኑም አስተዳደሩ በቀጣይ ሪፖርት በሚያቀርብበት ወቅት የተፈጠረው የሥራ እድል በምን ዘርፍ እንደሆነ ሊያቀርብ ይገባል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

የብድር አማራጮችን ከማስፋፋት፤ የተሰብሳቢ ገቢን ከማሳደግ እና የደከሙ ድርጅቶችን ከመደገፍ አኳያም መሥራት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

አጠቃላይ ሪፖርቱ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር መሻሻሎች እንዳሉት የተናገሩት ዋና ሰብሳቢው፤ የሴቶች የአመራር ተሳትፎ 30 በመቶ መድረሱን እንደጥሩ ጅማሮ በመውሰድ 50 በመቶ ለማድረስ ሊሠራ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ስለሺ ኮሬ (ዶ/ር) ኢንጂነር በበኩላቸው ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ጋር ተያይዞ የክር ግብዓትን ከህንድና ከቻይና ለማስገባት በርካታ የውጭ ምንዛሬ የሚወጣ በመሆኑ ይህን ለማስቀረት፤ በሀገር ውስጥ ጥራቱን የጠበቀ የጥጥ ምርት ለማምረት የሚያስችሉ ሥራዎች ሊሠራ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

ምክትል ሰብሳቢው ተቋሙ የኤሌክትሮኒክስ ክፍያን ለመፈጸም የሚያስችሉ ሥራዎች ላይ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ጥሩ ተግባር ነው ብለዋል፡፡

በመንግሥት የልማት ድርጅቶች እና ይዞታ አስተዳደር የስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ኤርሚያስ መብራቱ ሪፖርቱን ባቀረቡበት ወቅት እንደገለጹት፤ በ2016 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ለ15ሺህ 381 ዜጎች የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡ ይህም 91 በመቶ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ከተፈጠው የሥራ እድል 32 በመቶ የሚሆነው በኢንዱስትሪ ፓርኮች መሆኑን በመግለጽ፤ አጠቃላይ ከተፈጠረው የሥራ እድል የሴቶች ድርሻ 62 በመቶ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ዶክተር ኤርሚያስ እንደተናገሩት የልማት ድርጅቶችን ትርፍ በማሳደግ ረገድ 2 ነጥብ 24 ቢሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዶ 0 ነጥብ 81 ብሊዮን ብር ትርፍ ተገኝቷል፡፡

ይህም የእቅዱ 33 በመቶ እንደሆነ በመጥቀስ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር 40 በመቶ መቀነሱን ተናግረዋል፡፡

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እና ይዞታ አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ኃ/ሚካኤል እንደገለጹት በአስተዳደሩ ስር ከሚገኙ ዘጠኝ የልማት ድርጅቶች ሰባቱ ከፍተኛ ገቢ እያስገኙ ይገኛል፡፡

በዚህም የልማት ባንክ፤ የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት እና ሌሎች ድርጅቶች ካጋጠማቸው ኪሳራ ተመልሰው ከፍተኛ የትርፍ ክፍያ በማስገኘት ላይ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ምድር ባቡር እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ውጤታማ አለመሆናቸውን በማንሳት፤ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን በርካታ እዳ ያለበት መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ የእዳ ጫናው እንዲበዛ ያደረገው እዳው በወቅቱ ባለመከፈሉ ነው ሲሉም ተናግረዋል፡፡



ፎቶ - ገበየ ገብሬ

አቶ ኤሊያስ ኡመታ

## የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በኦሮሚያ ክልል ደረጃ በማያ ከተማ ይከበራል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- 18ኛው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል በኦሮሚያ ክልል ደረጃ ህዳር 26 ቀን 2016 ዓ.ም በማያ ከተማ በተለያየዩ መርሃግብሮች እንደሚከበር ጨፌ ኦሮሚያ አስታወቀ፡፡

የጨፌ ኦሮሚያ ምክትል አፈ ጉባኤ ኤሊያስ ኡመታ በዓሉን አስመልክተው ትናንት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳመለከቱት፤ 18ኛው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል በኦሮሚያ ክልል ደረጃ በማያ ከተማ በደማቅ ሁኔታ ይከበራል፡፡

በዓሉን ምክንያት በማድረግ ህዳር 25 ቀን 2016 ዓ.ም የፓናል ውይይት ይካሄዳል ያሉት ምክትል አፈ ጉባኤው፤ በዓሉ ህዳር 26 ቀን ደግሞ በማያ ከተማ የተለዩ ባህላዊና ታሪካዊ ሀብቶችን የሚያሳዩ ክንውኖች እንደሚኖሩ ጠቁመዋል።

የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል ከህዳር ወር መጀመሪያ አንስቶ በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች ላይ እየተከበረ እንደሚገኝ አመላክተው፤ በክልል ደረጃ የበዓሉን ሂደት የሚከታተል አስተባባሪ ኮሚቴ መቋቋሙን አስታውቀዋል።

በዓሉን በማስመልከት የዜግነት አገልግሎት፣ ቡሳ ጎኖፋና ባህላዊ ፍርድ ቤት ላይ የተጀመሩ ሥራዎች መጎብኘታቸውን የገለጹት ምክትል አፈ ጉባኤው፤ በተለይም በኢኒሼቲቭ የተያዙ የግብርና፣ ሌማት ትሩፋት፣ የጤና አገልግሎትን ጨምሮ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴና የቦንድ ግዢ ንቅናቄ በመደረግ ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

በዓሉ የተቋማት ሠራተኞችና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚያሳትፉ የውይይት መድረኮች መዘጋጀታቸውን ጠቅሰው የክልሉን ሕዝብ ባህል ማስተዋወቅ የሚያስችል ባዛር በማያ ከተማ መዘጋጀቱን አመላክተዋል፡፡

በዓሉ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት እንደሚከበር ተናግረው፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ በጂግጂጋ ከተማ ለሚከበረው በዓል የክልሉን ሕዝብ ባህል የሚወክሉ ልዑካን በመዘጋጀታቸውንና በዓሉ የክልሉን ሕዝብ ባህል ለማስተዋወቅ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ብለዋል፡፡

ኦሮሚያ በርካታ ብሔር ብሔረሰቦች ለብዙ ዘመናት ተቻችለው የሚኖሩበት ክልል መሆኑን የገለጹት ምክትል አፈ ጉባኤው፤ በዓሉ በክልሉ ከሚገኙ የተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች ጋር በመሆን ይከበራል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

18ኛው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል በሀገር አቀፍ ደረጃ "ብዝሃነትና እኩልነት ለሀገራዊ አንድነት" በሚል መሪ ሃሳብ በጂግጂጋ ከተማ እንደሚከበር ይታወቃል።

# በምርት ዘመኑ ከ42 በመቶ በላይ መሬት ላይ ሰብል ተሰብስቧል

**አዲሱ ገረመው**



አዲስ አበባ፡- በ2015/16 የመኸር እርሻ ምርት ዘመን ከተዘራው 17 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ ሰባት ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ (42 በመቶ) ያለ ሰብል መሰብሰቡን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።እስካሁን ከ 70 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ተገኝቷል፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ከበደ ላቀው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2015/16 የመኸር የምርት ዘመን 17 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር መሸፈን ተችሏል።ከዚህም እስካሁን ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ የደረሰ ሰብል ተሰብስቧል፡፡

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ ከብሔራዊ የሚቲዎ ሮሎጂ ኢንስቲትዩት በተሰጠው የአየር ትንበያ መሠረት ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ይከሰታል የሚል መልዕክትን በተደጋጋሚ ለአርሶ አደሩ ማድረስ ተችሏል።ተማሪዎችን ጨምሮ ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ ዘር የመሰብሰብ ሥራው በስፋት ተከናውኗል።በአሁኑ ወቅትም በባህላዊና በኮምባይነር ሰብል የመሰብሰብ ሥራው እየተከናወነ ይገኛል።

በመኸር አሰባሰቡ እስከ ኅዳር 17 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ብቻ በባህላዊ መንገድ ወደ 7 ሚሊዮን ሄክታር፤ በኮምባይነር ወደ 491ሺህ 322 ሄክታር በድምሩ ሰባት ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ያለ ሰብል ተሰብስቧል።

እንደ ግብርና ሥራ ሰብል ከተሰበሰበ በኋላ ይወቃል ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ ከተሰበሰበው ውስጥ ሁለት ነጥብ አራት ሄክታሩ ሰብል ተወቅቶ ከ70 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት መገኘቱን አስታውቀዋል።ከዚህ ውስጥ በኦሮሚያ ክልል ወደ 57 ሚሊዮን ኩንታል፤ እንዲሁም በአማራ ክልል ሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደተገኘ አስታውቀዋል።ቀሪው ሲወቃ ምርቱ እየጨመረ እንደሚሄድም ገልጸዋል።በአሁኑ ወቅት ሰብል የመሰብሰብ ሥራው ተጠናክሮ በመቀጠል በሁሉም ክልሎች እየተሠራ እንዳለም አቶ ከበደ ገልጸዋል፡፡

በምርት አሰባሰቡ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ተግዳሮት ሆኖ እንደቆየ በመግለጽ፤ በቅንጅት በተከናወነ ሥራ ቶሎ የደረሱ ሰብሎችን መሰብሰብ ተችሏል ነው ያሉት።በቀጣይም ፀሀያማና ደረቅ የአየር ንብረት ባለበት ወቅት ህብረተሰቡ ሰብሉን ቶሎ እንዲሰበስብ ምክረ ሃሳብ እንደተሰጠ አብራርተዋል።

# ዩኒቨርሲቲው ከ15 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ የህክምና ቁሳቁሶች ድጋፍ አገኘ

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ከዓለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን ሙብት (ግሎባል አልያንስ) ከ15 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ የህክምና ቁሳቁሶች ድጋፍ አገኘ።

የግሎባል አሊያንስ በኢትዮጵያ ተወካይ አቶ በፍቃዱ ዓባይ ድጋፉን ለጎንደር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት አስራት አፀደወይን (ዶ/ር) ትናትና አስረክበዋል።

በወቅቱ አስራት አፀደወይን (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ ድጋፉ ዩኒቨርሲቲው ለህብረተሰቡ የሚሰጣቸውን የህክምና አገልግሎቶች በተሻለ ሁኔታ ተደራሽና ቀልጣፋ በማድረግ ረገድ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል።

ድጋፉ ቀዶ ህክምና አገልግሎት መስጫዎችን፣ የህክምና አልጋዎች እና ዊልቸር ያካተተ መሆኑን ጠቁመው፤ ግሎባል አሊያንስ ያደረገው ድጋፍ ለዩኒቨርሲቲው በሚያስፈልገው ወቅት የቀረበ መሆኑ ልዩ ያደርገዋል ብለዋል።

ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከመንግሥት ጎን ሆነው የወገናቸውን ችግር ለመቅረፍ የሚያደርጉት ድጋፍ የሚያስመሰግን ነው ያሉት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት፤ ለተደረገው ድጋፍ አመስግነው ድጋፉ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል።

የግሎባል አልያንስ በኢትዮጵያ ተወካይ አቶ በፍቃዱ አባይ እንደገለጹት፤ ድጋፉ በህክምና ቁሳቁስ እጥረት ለተቸገሩ ወገኖች ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

ድርጅቱ ከተለያዩ ለጋሽ ግለሰቦችና ተቋማት የሚያሰባስባቸውን ሀብቶች ለኢትዮጵያውያን በማድረስ እያበረከተ ያለው ሥራ እንደሚቀጥል አቶ በፍቃዱ ተናግረዋል።

በአርቲስትና አክቲቪስት ታማኝ በየነ የሚመራው ግሎባል አሊያንስ ኢትዮጵያውያን በተቸገሩ ጊዜና ሥፍራ ቀዳሚ በመሆን ለሀገርና ለወገን የሚደርስ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው ሲሉ አስረድተዋል።

ለዩኒቨርሲቲው የተደረገው ድጋፍ የሰሜን ጎንደር አካባቢዎች ለመርዳት እንደሚያግዝም ጨምረው ገልጸዋል።

ግሎባል አልያንስ በተለያዩ ሀገራት ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ መንገዶች የተሰበሰቡ ሀብቶችን መልሶ ለኢትዮጵያውያን ማድረሱን ይቀጥላል ሲሉ ተናግረዋል።

ግሎባል አልያንስ ለዩኒቨርሲቲው ያስረከበው የህክምና መርጃ ቁሳቁስ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማህበረሰብ አባላትና ከእምወድሽ ፋውንዴሽን በተበረከተ ድጋፍ የተገኘ መሆኑ ተገልጿል።

# 28ኛው የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔ በዱባይ እየተካሄደ ነው

## - የኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራ መካነ ርዕይ ለተሞክሮ ቀርቧል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- 28ኛው የመንግሥታቱ ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔ (ኮፕ28) በትናንትናው ዕለት በተባበሩት ዓረብ ኢሚሬቶች መካሄድ ጀምሯል፡፡ ከጉባዔው አስቀድሞም የኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራን የሚያሳይ መካነ ርዕይ ቀርቧል፡፡

የኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራ መካነ ርዕይም ፕሬዚዳንት ሼህ ሞሀመድ ቢን ዛይድ አል ናህያን ከኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጋር በመሆን ጎብኝተዋል፡፡

ሼህ ሞሀመድ ቢን ዛይድ አል ናህያን፣ ኢትዮጵያ ለአየር ጠባይ ለውጥ መከላከል እያከናወነች ያለውን ተጨባጭ መፍትሄ ለማሳየት ያቀረበችውን የኢትዮጵያን የአረንጓዴ ዐሻራ መካነ ርዕይ በመጎብኘታቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ምሥጋና ማቅረባቸውን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት በማኅበራዊ ትስስር ገፁ አስታውቋል፡፡

በአረብ ኢምሬትሷ ዱባይ ትናንት መካሄድ የጀመረው ጉባዔው እስከ ታህሳስ 2 ቀን 2016 የሚቆይ ሲሆን፤ ከ130 በላይ ሀገራት መሪዎች እንደሚሳተፉበት ይጠበቃል።

# በመዲናዋ በቅርቡ ከፍተኛ የምርት አቅርቦት ይኖራል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ መግቢያ በሮች የሦስት የገበያ ማዕከላት ግንባታ በመጠናቀቁ በመዲናዋ በቅርቡ ከፍተኛ የምርት አቅርቦት እንደሚኖር የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ አስታወቀ። ቢሮው የተያዘው በጀት ዓመት ሩብ ዓመት አፈፃጸምን በሚመለከት ከወረዳ እና ክፍለ ከተማ ከሚገኙ አመራሮች ጋር ትናንት ተወያይቷል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ የንግድና ግብይት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ መስፍን አሰፋ ለመገናኛ ብዙኃን እንደገለጹት፤ በበጀት አመቱ የኑሮ ውድነትን ለማቅለልና የምርት አቅርቦት ችግሩን ለመፍታት የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል። በዚህም አምራቾችና ሸማቹ በቀጥታ ግብይት የሚፈፅሙባቸው ከታክስ ነፃ የሆኑ የቅዳሜና እሁድ የገበያ ቦታዎችን የማስፋት ሥራ ተሠርቷል።

በገበያው የኢንዱስትሪ ምርቶች በቀጥታ ከአርሶ አደሩና ከአምራች ኢንዱስትሪዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ለከተማዋ ነዋሪዎች እንዲቀርብ ተደርጓል ያሉት አቶ መስፍን፤ በመዲናዋ መግቢያ በሮች የሦስት የገበያ ማዕከላት ግንባታ በመጠናቀቁ በቅርቡ በመዲናዋ ከፍተኛ የምርት አቅርቦት ይኖራል ብለዋል።

እንደ አቶ መስፍን ገለፃ፤ በአሁኑ ጊዜ በመዲናችን እየተስተዋለ ላለው የኑሮ ውድነት ዋነኛ ምክንያቱ የምርት አቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም ነው። ይህንን ለመቅረፍ ከተማ አስተዳደሩ ስትራቴጂካዊ ሥራዎች እየሠራ ይገኛል። ለአብነትም በከፍተኛ በጀት በመዲናዋ መግቢያ በሮች ግዙፍ የገበያ ማዕከላትን ገንብቷል።

የሰብል ምርቶች ገበያ ማዕከላቱ በአቃቂ ቃሊቲ፣ በለሚ ኩራ እና በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተሞች



አቶ መስፍን አሰፋ

የተገነቡ ሲሆን፣ እነዚህም እየተስተዋለ ያለውን የኑሮ ውድነት ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ነው ያሉት አቶ መስፍን።

በእነዚህ የገበያ ማዕከላት የሚቀርቡ ምርቶች የመሸጫ ዋጋ ውጪ ካለው የምርቶች መሸጫ ዋጋ ከ 10 እስከ 15 በመቶ ቅናሽ ይኖራቸዋል ያሉት አቶ መስፍን፤ የእሁድ ገበያዎችም የኑሮ ውድነቱን ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ነው ብለዋል። በገበያው የሚቀርቡ ምርቶች ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑም እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

መንግሥት በተለያየ መልኩ የሚያቀርባቸውን መሠረታዊ ሸቀጦች ለህብረተሰቡ ለማድረስ እየተስተዋሉ ያሉ ብልሹ አሠራሮችን ለመቅረፍ በቴክኖሎጂ በተደገፈ መንገድ አገልግሎት መሰጠት መጀመሩንም ያብራሩት አቶ መስፍን፣ የኑሮ ውድነቱን ለመቀነስ የተለያዩ ሕግ የማስከበር ሥራዎች እየተሠሩ በመሆኑ ኅብረተሰቡ አስፈላ ጊውን ትብብር እንዲያደርግ እና በ 8588 ነፃ የስልክ መስመር ጥቆማ እንዲሰጥ ጥሪ አቅርበዋል።

በእለቱ ቢሮው በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ20ኛ ጊዜ በሀገራችን ደግሞ ለ19ኛ ጊዜ የሚከበረውን የፀረ ሙስና ቀንን አክብሯል።

# የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የማሻሻያ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እያዳበረ እንዲሄድ በተጨማሪም ዘመኑ ከደረሰበት ቴክኖሎጂ አኳያ የመልቲ ሚዲያ አማራጮችን በመጠቀም የጀመራቸውን ሥራዎች እንዲተገብር ማድረጉ ጠቃሚ መሆኑን አንስተዋል።

በተወሰነ ሀብት ቴክኖሎጂን በመጠቀም ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር ተገቢ መሆኑንም ከቋሚ ኮሚቴውና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት በማካሄድ ምላሽ እንዲያገኝ መደረጉንም አቶ ታገሰ አመልክተዋል።

ምላሽና ማብራሪያ የሰጡት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ እውነቱ አለነ፤ ተቋሙ በኢትዮጵያ ሕትመት ሚዲያ ዘርፍ ከፍተኛ ልምድና እውቀት ያለው መሆኑን አንስተዋል።የሚበረታቱ በርካታ የሪፎርም ሥራዎች መሠራታቸውንም ጠቁመዋል።

በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያው እጅግ መዘመን ምክንያት የህትመት ሚዲያው ሊገጥመው የሚችለው ፈተና ቀላል ባለመሆኑ በህትመት ዘርፍ ብቻ መቀጠሉ አዋጭ አለመሆኑን አንስተዋል።

‹‹አዲሱ የሚዲያ ዘመን ላይ ነን።ወቅቱ ከኢንተርኔት ጋር የተያያዘ በመሆኑ የመጡ አዳዲስ ለውጦች አሉ፣ ሂደቱም የሚዲያ መዋሃድ እንዲፈጠር፣ የሚዲያ ድንበርም እንዲጠፋ አድርጓል›› ሲሉ አንስተዋል።

ሁሉም ሚዲያዎች የተዋሃዱበት ዘመን ተፈጥሯል ያሉት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ፤ ይህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ፈተናም ዕድልም አምጥቷል ብለዋል፡፡

በዚህም ድርጅቱ ከህትመት ሥራው ሳይወጣ ሌሎች አማራጮችን እንዲጠቀም ማድረግ ተገቢ ነው ያሉት የተከበሩ አቶ እውነቱ፤ የሌሎች ሀገራት ልምድና ተሞክሮም የሚያሳየው ይህንኑ የተደጋገፈ ሥርዓት መሆኑንም በማንሳት አብራርተዋል።

በመሆኑም ኅብረ ብሄራዊ አንድነት እና ብሄራዊ መግባባት እንዲመጣ ድርጅቱ ከፍተኛ ልምድ ካካበተበት የህትመት ሚዲያ ሥራ በተጨማሪ የተለያዩ የይዘት የማሰራጫ አማራጮችን መጠቀም እጅግ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ጠቁመዋል።

ድርጅቱ ካለው ባህሪ የተነሳ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የግዢና የፋይናንስ ሥርዓትን ተከትሎ ማከናወን እና ሂሳቡን ማስመርመር ለተቋሙ ትልቅ ፈተና እየሆነ በመምጣቱ የመንግሥት የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር መርሆዎችን የተከተለ የራሱን አሠራር እንዲዘረጋ በአዋጁ ተደንግጓል። በዚህም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ማሻሻያ አዋጅ ማሻሻያ ቁጥር 1308/2016 ሆኖ በሙሉ ድምጽ ጸድቋል።

ምክር ቤቱ በተጨማሪም የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የአፍሪካ መድሃኒቶች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ስምምነት ረቂቅ አዋጅን ለማጽደቅ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብም መርምሮ አጽድቋል።

የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህልና ስፖርት ጉዳዮች ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይዘሮ ወርቀሰሙ ማሞ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳቡን ሲያቀርቡ እንዳሉት፤ የአፍሪካ ኅብረት አባል ሀገራት ጥራቱ፣ ደህንነቱና ውጤታማነቱ የተረጋገጠ መድሃኒት ለአፍሪካ ሕዝብ ጤና እና ደህንነት አስፈላጊ መሆኑን በማመን የአፍሪካ መድሃኒቶች ኤጀንሲን ማቋቋማቸውን ተከትሎ ኢትዮጵያም ስምምነቱን ተቀብላ ማጽደቋ አስፈላጊ መሆኑን አመልክተዋል።

የኤጀንሲው መቋቋምና ስምምነቱ መፈረሙ በአፍሪካ እየተከናወኑ ያሉ የመድሃኒት ቁጥጥር አሠራር ሥርዓቶችን ለማስተባበር፣ የኅብረቱ አባል ሀገራት፣ በክፍለ አህጉር ደረጃ የሚገኙ የኢኮኖሚ ማኅበረሰቦችን እንዲሁም የክፍለ-አህጉራዊ የጤና ተቋማትን ጥረት ለማጠናከር እንደሚያግዝም ነው ያብራሩት።

የቁጥጥር መመሪያ ማቅረብና ህመምተኞች በጥንቃቄ፣ ጥራቱን በጠበቀና ፍቱንነቱ በተረጋገጠ የመድኃኒት ምርቶችና የጤና ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል በመሆኑ እንዲሁም ለሕዝቡ ጥራቱና ደህንነቱ የተጠበቀ መድሃኒት እንዲዳረስ የሚያስችል መሆኑን በማመን ቋሚ ኮሚቴው በሙሉ ድምጽ አጽድቆታል።

# ኢትዮጵያ ብሪክስን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅሞች በማስጠበቅ ረገድ በዘላቂነት ለመሥራት የሚያስችል መደላድል ለመፍጠር ያለመ የምክክር መድረክ ትናንት ተካሂዷል።

በመድረኩ ንግግር ያደረጉት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ፤ ኢትዮጵያ ብሪክስን የተቀላቀለችው ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስጠበቅ ነው ብለዋል።

የብሪክስ አባል መሆን ለንግድ፣ ለኢንቨስትመንት፣ አማራጭ የልማት ፋይናንስ ምንጭን ለማስፋትና አጋርነትን ለማጎልበት ያግዛል ሲሉ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ጉልህ ተሳትፎ ስታደርግ የቆየች፣ ዓለም አቀፍ የጋራ ትብብርን በሚያመጡ ጉዳዮች ላይ ልምድ ያላትና ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ የምትንቀሳቀስ ሀገር መሆናንም አውስተዋል።

እንደ አምባሳደር ምስጋኑ ገለፃ፤ ብሪክስ ሁሉንም አይነት አመለካከት ያቀፈ ግማሽ የሚሆነውን የዓለም ሕዝብ የያዙ ሀገራት የተካተቱበት ስብስብ ነው። 30 በመቶ ያህል የዓለም ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴን የሚያካሂዱ ሀገራትም የሚገኙበት ኅብረት ነው።

በመሆኑም ኢትዮጵያ ይህን ስብስብ መቀላቀሏ የምትገኝበትን ቀጣና፣ አፍሪካን እና ዓለም አቀፍ ጉዳዮችን በተመለከተ ድምጿን ማሰማት የምትችልበት ተጨማሪ ዕድል የሚፈጥር ትልቅ የዲፕሎማሲ ስኬት ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ብሪክስን የተቀላቀለችው ማንንም ለማስደሰትና ለማስከፋት አይደለም ያሉት አምባሳደር ምሥጋኑ፤ አንዳንዶች እንደሚሉትም የፖለቲካ ካምፕ አይደለም የተቀላቀለችው ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ሀገር ከየትኛውም ጎራ የመወገን ፍላጎትም እንደሌላት ነገር ግን ብሔራዊ ጥቅሟን በሚያስከብር ማዕቀፍ ውስጥ ሁሉ ገብታ እንደምትሠራ አብራርተዋል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በመንግሥት በጀት በማይሸፈኑ ማህበራዊ ልማቶች ላይ ያላቸው ሚና ከፍተኛና የማይተካ መሆኑን ጠቅሰው፤ የኢትዮጵያን ገፅታ በመገንባት እና የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዋ ዓለም አቀፍ ዕውቅና እንዲያገኝ በማድረግ በኩልም ትልቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

ለወደፊቱም በአጠቃላይ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በማስጠበቅ ረገድ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በጋራ እንደሚሠሩ ተናግረዋል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ፋሲካው ሞላ በበኩላቸው፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በበርካታ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በጎ አስተዋጽኦ እያበረከቱ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

በብሪክስ አባልነት ጉዳይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ መፈጠሩ ማህበራቱ የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ እንደሚያስችል ገልጸዋል።

ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በተሳተፉበት መድረክ ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል መሆኗን በተመለከተ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ዘንድ ያለውን አረዳድ እንዲሁም ኢትዮጵያ ብሪክስን መቀላቀሏ የሚኖረውን ፋይዳ የዳሰሱ ሁለት ጥናታዊ ፅሑፎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

ኢትዮጵያ ብሪክስን ለመቀላቀል ያቀረበችው የአባልነት ጥያቄ በይፋ ተቀባይነት ያገኘው ከአራት ወራት በፊት በደቡብ አፍሪካ በተካሄደው የብሪክስ አባል ሀገራት 15ኛ ጉባዔ መሆኑ ይታወሳል። ከመጪው ጥር ወር ጀምሮም የብሪክስ ሙሉ አባል ትሆናለች።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የመመሪያው ተፈጻሚነት የሁሉንም አካላት ርብርብ ይሻል!

በከተማችን ከፍተኛ የሕዝብ ቅሬታ ምንጭ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ «የጫኝና አውራጅ ማኅበራት» ጉዳይ እንደሆነ የሚታወቅ ነው። ማኅበራቱ በየአካባቢው ያሉ ሥራ አጥ ወጣቶችን በሕጋዊ መንገድ ወደ ሥራ በማስገባት ለራሳቸው፤ ለቤተሰባቸው እና ለሀገራቸው አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ታስበው ወደ ተግባር የገቡ ናቸው።

እነዚህን በከተማዋ የሚገኙ ሥራ አጥ ወጣቶችን ወደ ሥራ ለማስገባት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በኩል የተወሰደው እርምጃ በወቅቱ ከጭነት ማውረድና መጫን ጋር በተያያዘ ይፈጠሩ የነበሩ ያልተገቡ ውጣ ውረዶችንና አለመግባባቶችን ሕጋዊ በማድረግ፤ ሥርዓት ማስያዝ እንደሚችልም በብዙዎች ዘንድ ታምኖበት ነበር።

ሁኔታዎች ግን ከታሰበው ይልቅ ወደ አልታሰበው እያመሩ፤ ነዋሪዎችን ላልተፈለገ ወጪና እንግልት ዳርገዋል። በየአካባቢው ለጸጥታ መደፍረስና ለአምባጓሮ ምክንያት ሆነዋል። በየሰፈሩም በማኅበራቱ ስም ለሕግና ለሥርዓት ተገዥ ያልሆኑ የመንደር የጎበዝ አለቃዎችንም ፈጥሯል።

የከተማዋ ነዋሪዎች በንብረታቸው ላይ የማዘዝ ሕጋዊ መብታቸውን ተነፍገው፤ በየሰፈሩ የተፈጠሩ የጎበዝ አለቆች በወደዱትና በፈቀዱት መንገድ ለመስተናገድ የተገደዱበት ሁኔታ ተፈጥሮ ቆይቷል። ችግሩም በጸጥታ አካላት ሳይቀር በቂ ትኩረት ባለማግኘቱ ነዋሪዎች ለከፋ ችግር ተዳርገው ቆይተዋል።

ችግሩ በተለይም በአዲስ አበባ ዙሪያ በሚገኙ የማኅበራትና የጋራ ቤቶች አካባቢ ጎልቶ ሲስተዋል የቆየ ነው፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች በተለያዩ ምክንያቶች ቤት ለመቀየር የሚገደዱ የከተማዋ ነዋሪዎች ከሚያስወርዱት /ከሚያስጭኑት ዕቃ ዋጋ የበለጠ የሚጠየቁበት ሁኔታም መፈጠሩም የችግሩን አሳሳቢነት የሚያመላክት ነው።

ዕቃዎችን ባልነው ዋጋ፣ ያለእኛ ማውረድ አይቻልም የሚሉት በማኅበር ስም የሚንቀሳቀሱ የየመንደር የጎበዝ አለቃዎች፤ ለሚሰጡት አገልግሎት ዋጋ ለመተመን ምንም ዓይነት ይሉኝታ የሌላቸው፤ ከምንም በላይ በማስፈራራትና በማስጨነቅ የጠየቁትን ለማስከፈል ራሳቸውን ያዘጋጁ ናቸው።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ በአዲስ አበባ አንድ ሺህ 78 በሕጋዊ መንገድ እና 550 ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የተደራጁ የጫኝና አውራጅ ማኅበራት ይገኛሉ። ሕጋዊዎቹን ትተን ሕገወጦቹን ብቻ እንኳን ለማየት ብንሞክር ችግሩ የቱን ያህል የገነነ እንደሆነ አመላካች ነው።

ይህንን የነዋሪዎችን ችግር ለዘለቄታው ለመፍታት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፤ የጫኝና አውራጅ ማኅበራት የአገልግሎት አሰጣጥን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል አዲስ መመሪያ ተግባራዊ ማድረጉን የከተማዋ ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ሰሞኑን አስታውቋል፡፡

እንደ ቢሮው ከሆነ፤ አዲሱ የመተዳደሪያ መመሪያ በጫኝ እና አውራጅ ሥራ ላይ ይነሳ የነበረውን ችግር በመፍታት ማኅበረሰቡ ሰላማዊና የንብረት ደህንነት የተረጋገጠ አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችል ነው፡፡

ማኅበራቱም በመመሪያው መሠረት ማኅበራቱ በተደራጁበት ዓላማ ብቻ በመሥራት ለማኅበረሰቡ ስጋት ሳይሆን የሰላማዊ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል፤ ሥራቸውን ሕግና ሥርዓት በተከተለ መልኩ መሥራት ከቻሉ ከኅብረተሰቡ ጋር የሥራ አጋርነት በመፍጠር ተጠቃሚ መሆን የሚያስችላቸውም ነው፡፡

መመሪያው ማኅበራትን ከማደራጀት ጀምሮ ከአገልግሎቱ ላይ የሚያጋጥሙ ቅሬታዎችን የሚፈታ፣ የሕግ ተጠያቂ የሚያሰፍን፣ ያለአግባብ ክፍያንና አስገዳጅ አሠራርን የሚያስቀር እንደሆነም አመልክቷል፡፡

አስተዳደሩ የጫኝና አውራጅ ማኅበራት ተጠሪነታቸው የከተማዋ ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ እንዲሆን ከማድረግ ጀምሮ፤ ለማኅበራቱ የሚተዳደሩበት አዲስ መመሪያ አዘጋጅቶ ወደ ሥራ መግባቱ ለችግሩ የሰጠውን ትኩረት አመላካች ነው። የነዋሪዎችን ቅሬታ ለመፍታት ያለውን ቁርጠኝነት የሚገልጽ ነው።

መመሪያው ከሁሉም በላይ የነዋሪዎችን በንብረታቸው የማዘዝ ሕጋዊ መብት ብቻ ሳይሆን፤ ለሚፈልጉት አገልግሎት መክፈል የሚገባቸውን ክፍያ የራሳቸውን አቅም ታሳቢ አድርገው መክፈል የሚያስችላቸውን አቅም የሚያጎናጽፋቸው ሊሆን ይገባል ።

ችግሩ አብሮን ለረጅም ጊዜ ከመቆየቱ የተነሳም በተለይም በየአካባቢው የነበሩ የጎበዝ አለቆች ሲሄዱበት የነበረው ሕገወጥ መንገድ፣ ሕጋዊ የሆነ ያህል ተቀብለውት የነበረ በመሆኑ የመመሪያው አፈጻጸም አልጋ በአልጋ ሊሆን እንደማይችል ይታመናል።

ከዚህ የተነሳ በተለይም የጸጥታ ተቋማት ችግሩ በአንድም ይሁን በሌላ በከተማዋ ሕጋዊነት ከማስፈን ጋር የተያያዘ የጸጥታ ጉዳይ ጭምር በመሆኑ ለመመሪያው ተፈጻሚነት ራሳቸውን በበቂ ደረጃ ማዘጋጀት እና ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በጫኝና አውራጅ ላይ ተስፋ ሰጪ ርምጃ

ኃይለማርያም ወንድሙ

ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ብዛት ያላቸው ዜጎች ሥራ ፍለጋ ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ፡፡ አጋጣሚና ዕድል በሰጣቸው የሥራ መስክም ተሰማርተው ዛሬን ለማሸነፍ ብሎም ነገን ብሩህና የተሻለ ለማድረግ ይተጋሉ።

ከዚህ ውጪም እዚሁ አዲስ አበባና ዙሪያዋ ያሉ ሥራ አጥ ወጣቶችን ወደ ሥራ በማስገባት፤ አምራች ኃይል ለማድረግ ባለፉት ዓመታት ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በዚህም ስኬታማ መሆን የተቻሉባቸው የሥራ መስኮች እንዳሉ ሁሉ የከሸፉና ከዚህም ባለፈ የችግር ምንጭ የሆኑም አሉ።

ከእነዚህ ውስጥ የዕቃ ጫኝና አውራጆች ጉዳይ አንዱ ነው። የከተማዋ አስተዳደር ሥራ አጥ ወጣቶችን ሥራ ለመፍጠር ካደረጋቸው ጥረቶች አንዱ እነዚህን ወጣቶች በማኅበራት አደራጅቶ ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረግ ነበር።

የሥራ አጥ ወጣቶቹ በማኅበር የመደራጀት ጉዳይ ለሥራው እውቅና በመስጠት በሕግና ሥርዓት እንዲመራ ለማስቻል እንደሚሆን ለመገመት ብዙም የሚከብድ አይሆንም። ሃሳቡም ሆነ ጅምሩ የሚበረታታ እና እውቅና ሊሰጠው የተገባ ስለነበር በብዙዎች ተበረታትቷል፤ እውቅናም አግኝቷል።

ብዙም ሳይቆይ ግን ሁኔታው ከታሰበው ይልቅ ያልታሰቡ ችግሮችን ይዞ በመምጣቱ፤ ለከተማው ነዋሪ ነገሩ ‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ›› ሆኗል። ሀይ ባይ ያጡ የሰፈር ጌቶች የሚፈለፈሉበት፤ ከሕግና ከሥርዓት እራሳቸውን አግዝፈው የሚያዩ የጉልበተኞች ስብስብ ሆኗል።

ሰዎች በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ ምክንያት ዕቃ ይገዛሉ፣ ይሸጣሉ፡፡ ቤት ይሸጣሉ ይለውጣሉ፡፡ ይከራያሉ፣ ያከራያሉ፡፡ ቤት ሲከራይ፣ ዕቃ ሲገዛና ሲሸጥ ደግሞ እንደ ክብደቱ መጠን መጫንና ማውረድ የግድ ነው፡፡ ገዥ የገዛውን ዕቃ በመኪና አስጭኖ ወደ መኖሪያ ቤቱ አልያም ወደ ንግድ ቤት ሊወስድ ይችላል፡፡ ሲደርስ ደግሞ በዕቃ አውራጆች ያስወርዳል፡፡

በቀድሞዎቹ የአዲስ አበባ የከተማ አካባቢዎች (እንደ መርካቶ ፒያሳ ..ወዘተ) በመሳሰሉ አካባቢዎች ዕቃ ገዝታችሁ ከፈለጋችሁ ራሳችሁ መጫን ማውረድ፤ አልያም ለፈለጋችሁት ሰው በፈለጋችሁት/ በተስማማችሁት ዋጋ ማስጫንም ሆነ ማስወረድ ትችላላችሁ፡፡ በጠቀስኳቸው ስፍራዎች ዕቃ ማውረድና መጫን የዕቃው ባለቤት ፍፁም ይሁንታ ያለበት ነው፡፡

ዕቃው ወይም ቁሱን የገዛው ሰውዬ /ሴትዮ መብት ነው፡፡ ጫኙና አውራጆቹ አሻፈረኝ ቢሉና የተጋነነ ዋጋ ቢጠይቁ ሥራውን ከማጣት ውጪ ሰሚ አይኖራቸውም፤ እናም ዕቃ ሲጭኑና ሲያወርዱ ሥራውን እንዳያጡ ዋጋ የሚጠሩት ተጠንቅቀው ነው፡፡

ይህ ለሕግና ለሥርዓት ተገዥነት ታዲያ በከተማዋ ዳርቻ ባሉ አካባቢዎች ማየት ‹‹ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ›› እንደሚሉት ተረት ነው፡፡ በአዲስ አበባ ዳርቻ አካባቢዎች እና በሸገር ዙሪያዎች ቤት ለቆ አልያም ተከራይቶ ዕቃውን በተሽከርካሪ የሚያስጭንና የሚያስወርድ ካለ በአካባቢው ካሉ ወጣቶች ጋራ አተካራ መግጠም፤ ክፈል አልከፍልም ጭቅጭቅ መግጠሙ የተለመደ ነው፡፡

በነዚህ አካባቢዎች ‹የጎበዝ አለቃ› የሆኑ ዕቃ ጫኛና አውራጆቹ፤ ዕቃዎችን ለማውረድ ሆነ ለመጫን በአስር ሺዎች ብር የሚጠይቁበት ሁኔታ ስለመኖሩም የአደባባይ ምስጢር ሆኗል፡፡ አንዳንዴ ከሚያወርዱት ዕቃ ዋጋ በላይም ሊጠይቁ ይችላሉ። ይሉኝታ የሚባል ነገር የለም።

ክስተቱ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ባሉባቸው አካባቢዎች የበዛ ነው፡፡ ቤት ለመከራየት አልያም ለመልቀቅ ዕቃ በሚያስጭኑና በሚያወርዱ ቤተሰቦች ላይ በብዛት ማየት የተለመደ ሲሆን፤ እነዚህ አካባቢዎች ጫኝና አውራጅ እንዳሻው የሚሆንበት፤ ፖሊስና የሚመለከታቸው አካላት ይህንን ሥርዓተ አልበኝነት ለመግታት ሲንቀሳቀሱ የማይታዩባቸው ናቸው።

> ኅብረተሰቡ (ነዋሪው) ለሚያገኘው አገልግሎት በአቅሙ መክፈል የሚያስችል፤ ሥራውን አክብሮ በሕግና ሥርዓት መሥራት የሚችል ኃይል መፍጠር የሚያስችል ሊሆን እንደሚችልም ይጠበቃል። መመሪያውን በጠንካራ ዲሲፕሊን ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ ሥርዓተ አልበኝነትን ለመቀነስና ለመቆጣጠር የሚረዳ በመሆኑ ይበል የሚያሰኝ ነው

ይህ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ያሉ ወላጆችና ነባር ነዋሪዎች ከመዝረፍ ያልተለየውን ማን አለብኝነት ተው! ብለው ማስቆም የሚያስችል አቅም የላቸውም፡፡ በየአካባቢዎቹ የሚገኙ የሕግ አካላትና ተቋማት ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ሲያፈላልጉ አይታይም።

በቅርቡ በኮዬ ፈጬ ከሚገኙ የጋራ መኖሪያ ቤቶች መካከል ቤት የደረሰው አንድ የትምህርት ሚኒስቴር ወዳጄ በአዲስ ከተማ ከተከራየው የግል ቤት ለቆ በቤቴ እየኖርኩ ቀስ በቀስ አድሳለሁ በሚል ወደ ተጠቀሰው ቦታ ዕቃውን ጭኖ ሄዶ ነበር፡፡ ዕቃውን ለማውረድ ግን 30 ሺህ ብር ካልከፈልክ አታወርድም ብለው አሻፈረኝ እንዳሉት አጫውቶኛል፡፡

በስንት ጭቅጭቅ ልመና 15 ሺህ ብር ለመክፈል ተገዶ ዕቃውን እንዳወረዱለት በቅሬታ ነግሮኛል፡፡ እኔ ይህን አልኩ እንጂ መሰል ክስተቶች በየጊዜው በየአካባቢው ይደመጣሉ፡፡ ይህ ከሁለት ዓመት በፊት የነበረው ከአምስትና 10ሺ ክፍያ አድጎ ተመንድጎ አሁን ከ30 ሺህ እስከ 50 ሺህ ብር ደርሷል፡፡

ይሁንና አሁን አሁን ሥርዓተ አልበኝነትና ማን ይነካኛል ዓይነት ጨዋታ ሊቀይር የሚያስችል ተስፋ ሰጪ ጅማሮ እየታየ ይመስላል፡፡ ለዚህም የአዲስ አበባ ሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ የማኅበረሰቡን መብት ሊያስጠብቅና ቀደም ሲል ሲታዩ የነበሩ የጫኝና አውራጅ አሠራር ችግሮችን ሊፈታ የሚችል አዲስ መመሪያ ማዘጋጀት እንደቻለ ኅዳር 1 ቀን 2016 ዓ.ም አስታውቋል። ነገሩ በጥቂቱም ቢሆን ለሕዝቡ እፎይታን ሊፈጥር እንደሚችል ይታመናል፡፡

ይህ መመሪያ፤ ማኅበረሰቡ ቅሬታ ሲያነሳበትና ሲማረርበት የነበረንና የኖረን ችግር ሥርዓት የሚያሲዝ፣ ነዋሪው በነፃነት ንብረቱን ለመጫንና ለማውረድ የሚያስችል እንደሚሆን ይታመናል። በየሰፈሩ ያሉ ከሕግና ሥርዓት በላይ የሆኑ ‹የጎበዝ አለቆችን› ከሕግ በላይ እንዳልሆኑ የሚያሳይ እንደሚሆን ይታሰባል፡፡

ኅብረተሰቡ (ነዋሪው) ለሚያገኘው አገልግሎት በአቅሙ መክፈል የሚያስችል፤ ሥራውን አክብሮ በሕግና ሥርዓት መሥራት የሚችል ኃይል መፍጠር የሚያስችል ሊሆን እንደሚችልም ይጠበቃል። መመሪያውን በጠንካራ ዲሲፕሊን ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ ሥርዓተ አልበኝነትን ለመቀነስና ለመቆጣጠር የሚረዳ በመሆኑ ይበል የሚያሰኝ ነው።

# የጦርነት- የኢኮኖሚ ቀውስን እንደ ማሳያ

**ሰው መሆን**

የሕዝብ እንደራሴዎች የጠቅላይ ሚኒስትሩን ማብራሪያ የሚያዳምጡበት ስድስተኛ መደበኛ ጉባኤ ለመከታተል ተሰይሜያለሁ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኢኮኖሚ፣ ሰላም፣ ግብርና፣ መሠረተ ልማት እና ሌሎችም ዘርፎች ላይ መንግሥታቸው እየሠራ ያለውንና ለመሥራት ያሰበውን ጉዳይ እንደተለመደው ያብራራሉ። እንደራሴዎቹም እኔም ጆሯችንን ስል አድርገን እናዳምጣቸዋለን።

የመንግሥታቸውን ጥረት፣ የሚያጋጥማቸውን እንቅፋት፣ የማኅበረሰቡን መረዳትና ትእግስት ማጣት፣ የተቃዋሚዎችን ጉድለት፣ ነፍጥ ያነገቡ ተቃዋሚዎች አመፅና በሰላም ለመፍታት የሚደረግ ጥረት፣ የኑሮውን ውድነት፣ የትርክታችን መዛባት፣ የቸገረንን፣ ያጣነውን፣ ያገኘነውን፣ የሆነልንን እያንዳንዱን ጉዳይ በዝርዝር ከመንግሥታቸው አቋም አንፃር እየተነተኑልን ነው። በዚህ መሀል ነው አንድ ንግግራቸው ትኩረቴን የወሰደው። ንግግሩ ከዚህ የሚከተለውን ይዘት ይይዛል።

«የካፒታል በጀታችንን ወይንም የልማት ፕሮጀክቶቻችንንም አጥፈን ቢሆን ኢትዮጵያን ለማዳን ዝግጁ ነን» የሚል ግርድፍ መልዕክት የያዘ ነው። ይህ ንግግር በጊዜው የእኔን ትኩረት ከመያዝ ባለፈ ዛሬም በስፋት በዚህ ገፅ ላይ ሃሳቤን እንድሰነዝር የገፋፋኝ ጉዳይ ሆነና ወደ እናንተ በድጋሜ ይዤው መጣሁ።

ጦርነት፣ ግጭት፣ ሥርዓት አልበኝነት ለኅብረተሰብ ሰላም መደፍረስ ምክንያት ናቸው። ከዚህ ባለፈ የሀገር ኢኮኖሚን በማድቀቅ፣ የትውልድን ሞራል በማላሸቅ፣ መሠረተ ልማትን በማውደምና ራዕይ አልባ ሀገር በማዋለድ ወደር አይገኝላቸውም። በዘመናት ሂደት የተገነባ ሥልጣኔ፣ ኢኮኖሚና አምራች ኃይል በአንድ ሳምንት ጦርነት ድራሹን ማጥፋት ይቻላል።

የጠፋውን ለመተካት፣ የወደመውን ለመመለስ ግን ዳግም ዘመናት የሚጠይቅ ነው። ለዚህ ነበር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለእንደራሴዎቻቸውና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደርግን እንደ ምሳሌ አንስተው በህልውና ጉዳይ «ፕሮጀክቶችንና የልማት አጀንዳዎቻችንን ለማጠፍ አናቅማማም» በማለት ሲናገሩ ንግግራቸው ሙሉ ለሙሉ ትኩረቴን የወሰደው። በዚህ ምክንያት ነበር በዛሬው ርዕሰ ነገሬ የጦርነትን አስከፊ የኢኮኖሚ ጫናና የውድቀት ገፅታ ለመመልከት የወደድኩት።

ጦርነት ውዱን የሰው ልጅ ሕይወት ከመቅጠፉ በላይ ኪስን አራቁቶ ከድህነት ወለል በታች እንደሚሰድድ ግልፅ ነው። የልማት አጀንዳዎቻችንን አጥፈን ወደ ጦርነት እንድንገባ የሚያስገድዱን ጉዳዮች ሲፈጠሩ ደግሞ የዛሬን ሳይሆን የመጪውን ትውልድ ተስፋ ጭምር የሚገድል ነው።

ይህንን ጉዳይ በዝርዝር ለመገንዘብ እንዲረዳን ጦርነት በኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሰውን ጫና ከዚህ እንደሚከተለው ለመመልከት እንሞክር። ስለ ጉዳዩ ጥልቅና ግልፅ መረዳት እንድናገኝ ከራሳችን ጉዳዮችም ወጣ ብለን ዓለም አቀፍ አንድምታውን ጭምር ማየት ጠቃሚ ይመስለኛል።

ጦርነት የማይተካውን የሰው ሕይወት ከመቅጠፍ ያለፈ አጥፊ አቅም ያለው ነው። በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ጫና ከማሳደር አልፎ የዋጋ ግሽበት (inflation) ይፈጥራል። ለዚህ ጥሩ ማሳያው የዩናይትድ ስቴት (አሜሪካ) የእርስ በእርስ ግጭት ጥሩ ማሳያ ይሆናል። በእርግጥ እሩቅ ሄደን ምሳሌ ለማንሳት የሚያስገድድ የመረጃ እጥረት ያለብን ባይሆንም ግን እናንሳው።

አሜሪካ በወቅቱ (during civil war) የነበረውን ጦርነት ለመቋቋም በማያስችል የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ገብታ ነበር። ይህ ችግር ደግሞ ለተዋጊው ኃይል ደሞዝ ለመክፈል ጥሬ ዶላር እስከ ማተም ያደረሰ ጫና ፈጥሯል። በኢኮኖሚ ውስጥ የተረጨው ገንዘብ ደግሞ የዶላርን የመግዛት አቅም ያዳከመ መካከለኛ ገቢ ያለውን ዜጋ በፋይናንስ ተቋማት ውስጥ ያጠራቀመውን ገንዘብ ዋጋ ያሳጣ ሆኖ አልፏል።

**ጦርነት፣ ግጭትና ሥርዓት አልበኝነት እንኳን በድህነትና ለማደግ በሚደረግ መፍጨርጨር ውስጥ ያለ ሀገር ገብቶበት ይቅርና ከፍተኛ ኢኮኖሚ ያላቸውም ጭምር ለክፍለ ዘመናት የገነቡትን ሀገር በአንድ ምሽት የመናድ አቅም አለው**

ሂደቱ ዶላር ዋጋ እንዲያጣ፣ ገበያ ላይ ያለው ምርት ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ በማድረጉ ምክንያት ለቀውስ ርሃብና ትርምስ (cost-push inflation) የዳረገ ነበር። የጦርነት አስከፊነት ከታየባቸው ጊዜያት ውስጥ የእርስ በእርስ ግጭቱ በታሪክ መዝገብ ላይ እንዲሰፍር አድርጎታል።

ጥሪታችንን አሟጠን የልማት ሥራዎቻችንን አቋርጠን በጭፍን የምንገባበት ጦርነት አጥፊ ነው ስንል በምክንያት ነው። ጦርነት፣ ግጭትና ሥርዓት አልበኝነት እንኳን በድህነትና ለማደግ በሚደረግ መፍጨርጨር ውስጥ ያለ ሀገር ገብቶበት ይቅርና ከፍተኛ ኢኮኖሚ ያላቸውም ጭምር ለክፍለ ዘመናት የገነቡትን ሀገር በአንድ ምሽት የመናድ አቅም አለው።

እዚህ ጋር «እንኳን ዘንቦብሽ እንዲሁም ጤዛ ነሽ» የሚለውን ብሂል ማስታወስ ተገቢ ነው። የጠቅላይ ሚኒስትሩ «በዶላር ከምንገዳደል በሃሳብ እንገዳደር» በማለት ያስቀመጡትንም አማራጭ ማጤን ይበጃል (ይህ ምክረ ሃሳብ መንግሥትንም ነፍጥ ያነገቡትንም ኃይሎች ይመለከታል)።

«ጦርነት አውዳሚ ነው» ስንል በምክንያት ነው። በእርግጥ ከጦርነት የሚያተርፉ ሀገራት፣ ካምፓኒዎች መኖራቸው ሀቅ ነው። የጦርነት ቴክኖሎጂ ሸጠውና ግጭት ጠምቀው ረብጣ ገንዘብና ጠንካራ ኢኮኖሚ የሚገነቡ አሉ። እኛ ግን መረዳት ያለብን በሃሳብ ልዩነት የምንገባበት አውዳሚ አማራጭ ሕይወታችንን ከማስከፈል ተሻግሮ የመጪውን ትውልድ ተስፋ እንደሚያጨልም ነው።

በእርግጥ የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ በልዩ ልዩ ምክንያት ጫና ውስጥ ሊገባ ይችላል። ግሽበትም ይጠበቃል። የኢኮኖሚ ባለሙያዎች እንደሚሉት ከግሽበት የሚያመልጥ አይኖርም። ይሁን እንጂ ፈቅደንና ግልፍተኛ ሆነን የምንጭረው ጦርነት የሚያስከትለው ጫና ከግሽበት የተሻገረ ቀውስ (hyperinflation) ነው።

ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ሀንጋሪና አውስትራሊያ ያስመዘገቡት ከቁጥጥር ውጪ የሆነ ግሽበት (hyperinflation) ነው። በሀንጋሪ ለ13 ወር የዘለቀው የገንዘብ የመግዛት አቅም መዳከምና የምርት እጥረት እንዲሁም በመንግሥት የፋይናንስ ተቋማት እምነት መጥፋት የተከሰተው በጦርነት ምክንያት ነበር። ታሪክም ይህንን ቀውስ በመዝገቡ አስፍሮት አልፏል።

በጦርነት ምክንያት ምርት ቢኖር እንኳን አቅርቦት ይስተጓጎላል። መንገዶች፣ የንግድ መስመሮች፣ ወደቦችና ሌሎች የግንኙነት ሰንሰለቶች ይበጠሳሉ። በዚህ ምክንያት ዋጋ ይንራል። የዓለማችን ከፍተኛ ስንዴ ላኪ ሀገራት የሆኑት ሩሲያና ዩክሬን ጦርነት ውስጥ በመሆናቸው ብቻ ያመረቱት እልፍ ስንዴ በመጋዘን ውስጥ የነቀዝ እራት እንዲሆን ተፈርዶበታል።

በዓለማችን ላይ ኮሽ ባለ ቁጥር ጣራ የሚነካው የድፍድፍ ነዳጅ ዋጋም የዚሁ ማሳያ ነው። ለጉዳያችን ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር 1990 የተከሰተው የገልፍ ጦርነት (gulf war) ነው። በጊዜው በዓለም ገበያ ላይ 21 ዶላር የነበረው አንድ በርሜል ድፍድፍ ነዳጅ ከእጥፍ በላይ ጨምሮ 46 ዶላር ደርሶ ነበር።

ይህ እንግዲህ ከዛሬ 33 ዓመት በፊት የነበረ ማሳያ ነው። ዓመት የተሻገረው የሩሲያና ዩክሬን ጦርነትን ትተን እንኳን በመካከለኛው ምሥራቅ በሀማስና እሥራኤል መካከል የተቀሰቀሰውን ጦርነት በምሳሌነት ብናነሳ የነዳጅ ዓለም አቀፍ ገበያን በስድስት በመቶ እንዲጨምር እንዳደረገ እንገነዘባለን። ይህ ሁሉ የጦርነት፣ የግጭትና የቀውስ ዳፋ ነው።

ጦርነት የሚያመጣው ቀውስ በዚህ የሚያበቃ አይደለም። ከዚህም የከፉ በርካታ ፈተናዎችን ይደቅናል። ጦርነት ቀድሞ የነበረን የመንግሥት ዕዳ ከመክፈል ይልቅ እንዲባባስ ይዳርጋል። የበለጠ የመበደር ፍላጎት ያሳድራል። ትውልድ የበለፀገ ሳይሆን በዕዳ የታጨቀ ሀገር እንዲረከብ ያስገድዳል።

ኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከፍተኛ የዕዳ ጫና ካለባቸው ሀገራት አንዷ እንደሆነች መረጃዎች ያሳያሉ (እንደ መንግሥት በሀገር ውስጥ ከብሔራዊ ባንክ የሚበደረውን ሳይጨምር)። የልማት ሥራዎች ላይ ማተኮር ከተቻለ እና ዕዳን መክፈል ያን ያህል ላያስቸግር ይችላል።

ነገር ግን በጦርነት ውስጥ ሆኖ ዕዳን መክፈል የማይታሰብ ነው። እንዲያውም ለተደራራቢ የብድር ጫና ይዳርጋል። ለዚህ አሁንም ወደ ሁለተኛው ዓለም ጦርነት ተመልሰን ተጨባጭ የታሪክ እውነታዎችን እንመልከት።

በሁለተኛው ዓለም ጦርነት (World War II) ቀዳሚ ተሳታፊ የነበረችው ዩናይትድ ኪንግደም እዚህ ጋር ቁንጅ ምሳሌ ትሆናለች። የሀገሪቱ መንግሥት ብድር (national debt) የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ማብቂያ ላይ በ150 በመቶ አድጎ ነበር። ይህ በ1950ዎቹ በከፍተኛ ሁኔታ አድጎ 240 በመቶ ደርሶ ነበር።

ዩናይትድ ኪንግደምም ከዩናይትድ ስቴት ብቻ ለጦርነት ፍጆታ የወሰደችውን ብድር ለመመለስ ከ20 ዓመት በላይ ፈጅቶባታል። ከዚህ በተፃራሪ አሜሪካ ለእንግሊዝ የጦር መሣሪያና ቴክኖሎጂ በመሸጥ አትራፊ ነበረች።

የጦርነት አስከፊነትን ደጋግሞ ማስመር ያስፈልጋል። ጦርነት በቁጥር ስሌት ውስጥ የማይገባውን ውዱን የሰው ልጅ ሕይወት ከማስገበሩም ባሻገር ብዙ ጥፋት ይዞ ይመጣል። ከዚህ ውስጥ ደግሞ ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ የመልሶ ግንባታ ሥራ (መሠረተ ልማት) አንዱ ነው።

«የቸኮለች አፍሳ ለቀመች» እንደሚባለው ብሂል በጦርነት ውስጥም ውድመት ከደረሰ በኋላ የጠፋውን መልሶ ለመሥራት ከፍተኛ አቅም ይጠይቃል። ለሌሎች የልማት ሥራዎች እና ኢኮኖሚ ጫና ማቃለያዎች ይውል የነበረ ሀብት የግዴታ ለመልሶ ልማት እንዲውል ያስገድዳል። በቅርቡ በሀገራችን በሰሜኑ ክፍል የተነሳው ጦርነት ያደረሰውን ኢኮኖሚ ጫናና የጠየቀው የመልሶ ግንባታ ወጪ ልብ እንበል።

የእርስ በርስ ጦርነት በሀገሮች ኢኮኖሚ እድገት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል። ኢትዮጵያን ጨምሮ የእርስ በርስ ጦርነት የሚያጋጥማቸው ሀገሮች በቱሪዝም፣ በውጭ ኢንቨስትመንትና በሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ውድቀት ያስከትልባቸዋል። የሀገር ውስጥ ምርት እድገት (GDP) እና የሕይወት ዘመን ቆይታ (Life expectancy) ዝቅተኛ እንዲሆን ምክንያት ነው።

ኦክስፋም ዩኒቨርሲቲ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2007 «የጠፉት የአፍሪካ ቢሊዮኖች» (Africa's missing billions) በሚል በሠራው ጥናት በአፍሪካ ሀገራት በጦርነት ምክንያት የሚወድመው ሀብትና ንብረት ለእርዳታ በምዕራባውያንና በአደጉት ሀገራት በምፅዋትነት ከሚገባው እኩል እንደሆነ ይፋ አድርጎ ነበር።

ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ በተፈጥሮ ሀብት የታደለች ሀብታም ሀገር ብትሆንም ያንን ግን በተደጋጋሚ በሚደረጉ ጦርነቶች ልትጠቀምበት አልቻለችም። የዜጎቿን ሕይወትም አልታደገችበትም። በከባድ ጦርነት ውስጥ አልፋለች። ጦርነቱ ወደ 4 ሚሊዮን ለሚጠጉ ሰዎች ሞት ምክንያት ከመሆኑም ባሻገር 9 ቢሊዮን ፓውንድ ወይም ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርቷ 29 በመቶው ወጪ እንድታደርግ አስገድዷታል።

ለዚህ ነው «ጦርነት» በየትኛውም መመዘኛ ቢታይ መጥፎ እንጂ ጥሩ ጎን የለውም የምንለው። ለዚህ ነው ወደ ግጭት ከማምራታችን በፊት (አፍስሰን ከመልቀማችን አስቀድመን) የሰላም አማራጮችን አሟጠን መጠቀም ይገባናል የምንለው። ለዚህ ነው ጠቅላይ ሚኒስትራችን ለእንደራሴዎቻቸው የሰላምን ጥቅም፣ የድርድርን አስፈላጊነትና በጠረጴዛ ዙሪያ ልዩነትን የመፍታት ምርጫን እንደ ተሻለ ሃሳብ ሲያቀርቡ ትኩረታችንን የወሰዱን። እርሳቸው እንዳሉት «በዶላር ከመገዳደል በሃሳብ መገዳደሩ» እንደሚበጅ የምናምነው። ሰላም!

# ለሕፃናቱ እፎይታን፤ ለቤተሰብ ተስፋን የሰጠው ሰዋዊ ተግባር

በኃይሉ አበራ

ሕጻን የአብስራ ሳሙኤል፤ ለአምስት ዓመታት ወረፋ ጠብቆ ከሕመሙ ሊፈወስ የልብ ቀዶ ሕክምና አግኝቷል። የአብስራ ሳሙኤል እናት ወይዘሮ ወጋየሁ አለፈ ልጃቸው ገና የሁለት ዓመት እድሜ እያለ ጀምሮ ሌሊት ላይ በሚያጋጥመው ሕመም የመተንፈስ ችግር እየገጠመው በብዙ ሲቸገሩ እንደነበር ያስታውሳሉ። በዚህ ምክንያትም በተለያዩ ሃይማኖታዊ ቦታዎች በመሄድ ልጃቸው የአብስራ ፍጹም ጤናማ እንዲሆን አምላካቸውን ተለማምነዋል።

ይሁንና ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ ግን ሕመሙ የልብ ችግር እንደሆነ በሕክምና ከተረጋገጠ በኋላ በልብ ህሙማን ማዕከል የሕክምና ክትትል ሲደረግለት ቆይቶ ደጋግ ልቦች ባደረጉት ድጋፍ ሕክምናውን ማግኘት ችሏል። ላለፉት አምስት ዓመታትም በየሶስት ወሩ እና በየስድስት ወሩ ክትትል ሲደረግለት ቆይቶ ዛሬ ላይ የልብ ቀዶ ሕክምና ማድረግ ችሏል።

በአሁን ወቅትም ሕጻን የአብሥራ ከአምስት የስቃይ ዓመታት በኋላ በተደረገለት የልብ ቀዶ ሕክምና በጥሩ ጤንነት ላይ መሆኑን ወላጅ እናቱ ወይዘሮ ወጋየሁ በደስታ ገልጸዋል። ‹‹አንድን ሕጻን ሕይወት መታደግ በምድርም በሰማይም ጽድቅ ነው›› የሚሉት ወይዘሮ ወጋየሁ፤ በተመሳሳይ ወረፋ እየተጠባበቁ የሚገኙ በርካታ ሕጻናት መኖራቸውን ጠቁመው ወላጆች በጽናት እንዲጠብቁና ልጆቻቸው ደህና እንደሚሆኑ መክረዋል። በኢትዮጵያ ልብ ሕሙማን መርጃ ማዕከል የሚሰሩ ሠራተኞችን ጨምሮ ለማህበሩ ድጋፍ ለሚያደርጉ ተቋማትና ግለሰቦች ጭምር የላቀ ምስጋናም አቅርበዋል።

ከአምስት ዓመታት ክትትል በኋላ ለልጃቸው የልብ ቀዶ ጥገና ለማድረግ እየተጠባበቁ ያገኘናቸው አቶ ኤፍሬም ተድላ ሌላኛው ተስፋ ያገኙ ወላጅ ናቸው። የአምስት ዓመቱ ሕጻን ዮናታን ኤፍሬም ወላጅ አባት አቶ ኤፍሬም ከድሬዳዋ የመጡ ሲሆን፤ ዮናታን የልብ ታማሚ መሆኑ የታወቀው በተወለደ ገና በአምስት ወሩ እንደነበር አስታውሰው፤ ከድሬዳዋ አዲስ አበባ በየሶስት ወሩ ለክትትል ሲመላለሱ መቆየታቸው ብዙ ዋጋ ያስከፈላቸው መሆኑን አንስተው፤ አሁን ግን ወረፋ ደርሷቸው ልጃቸው የልብ ቀዶ ሕክምና ሊያደርግ የሰዓታት ዕድሜ የቀረው በመሆኑ ልባቸው በተስፋ ተሞልቷል። ድካማቸው ቀሏል። ለዚህም የማዕከሉን ሠራተኞችና አጋር አካላትን በሙሉ በማመስገን ሌሎችም ሕጻናትም መልካም ዕድል እንዲገጥማቸው ተመኝተዋል።

በልብ ሕሙማን ህጻናት መርጃ ማእከል ተገኝተው ጉብኝት ያደረጉት የልማት ባንክ የሥራ ኃላፊዎች የማዕከሉን መሠረታዊ ችግሮች በመረዳት የአቅማቸውን ለማገዝ ቃል የገቡት ልክ የዛሬ ዓመት ነበር። ‹‹ቃል ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ›› እንዲሉ አበው በገቡት ቃል መሠረት ለሕክምና ሥራው ያስፈልጋሉ የተባሉትን ድጋፎች ይዘው በማዕከሉ ተገኝተዋል።

ድጋፎቹም 31 ሚሊየን ብር ዋጋ ያላቸው ለቀዶ ሕክምና የሚያገለግሉ ቁሳቁስ ናቸው፤ እነዚህ ቁሳቁስ ቢያንስ ለ250 የልብ ሕሙማን ሕጻናት ቀዶ ሕክምና አገልግሎት መስጠት እንደሚያስችሉ የማዕከሉ የሥራ ኃላፊዎች ይገልጻሉ። የዚህ ድጋፍ አድራጊ ተቋም የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ነው።

የሕክምና ቁሳቁሱን ለማዕከሉ ኃላፊዎች ያስረከቡት የልማት ባንኩ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው ባደረጉት ንግግር ባንኩ ከሥራዎቹ አንዱ የሰው ልማት መሆኑን አስታውቀዋል። የሀገራዊ ልማቶች ሁሉ መሠረት ሰዋዊ ልማት መሆኑን የተናገሩት አቶ ዮሐንስ፣ ልማት ባንክ ባደረገው በዚህ ድጋፍ ለምንወዳቸው ሕፃናት መድረስ በመቻሉ እርካታ ተሰምቶታል ሲሉም ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የኢትዮጵያን ልማት ማምጣት በሚችሉ ሕጻናት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል። ተምረው፣ የሚፈለገው ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ጤናቸው ሊጠበቅ ይገባል።

በተለይም የልብ ሕክምና ውስብስብ እና የተለየ ስፔሻላይዜሽን እንደሚፈልግ ጠቅሰው፣ የልብ ሕክምና አገልግሎት በሀገራችን ባልነበረበት ወቅት እናቶች




ልጆቻቸውን ለማሳከም አቅም በማጣታቸው ሳቢያ ብዙ ተፈትነዋል፤ ልጆቻቸው እጃቸው ላይ ይሞቱባቸውም ነበር በማለት አስታውሰዋል።

የልብ ሕሙማን ሕጻናት መርጃ ማዕከል መስራች የሆኑት ዶክተር በላይ አበጋዝ ይህ ማዕከል እንዲመሰረት ላደረጉት ጥረት ሊታሰቡ እንደሚገባም አስታውቀዋል። ዶክተር በላይ ይሄንን ተነሳሽነት ወስደው ሕክምናው ወደ ሀገሪቱ እንዲመጣ በማድረግ አንድ ሕፃን ወደ ውጭ ሀገር ወስዶ ለማሳከም በመቶ ሺዎች ብር ያስፈልግ የነበረውን አገልግሎት በሀገር ውስጥ መስጠት የሚያስችል ሥራ ሰርተዋል፤ ለዚህም የልማት ባንክ ማኔጅመንት እና ሠራተኞች ዶክተር በላይን በእጅጉ ያመስግናሉ ነው ያሉት።

‹‹ዶክተር በላይ ሁሌም ሊታሰቡ ይገባል፤ ፎቶግራፋቸም እዚህ መታየት ነበረበት›› ሲሉም አስገንዝበው፣ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎችን ማግኘት የሚቻለው ለሰዎች የምንሰጠው ክብር ሲኖር ነው ብለዋል።

እንደሳቸው ዓይነት ሰዎች ወደፊትም የኢትዮጵያን ችግር በመፍታት ፈር ቀዳጅ ሆነው ያግዛሉ። መሰል ሥራዎችን መሥራት እና ማስፋት ይገባል፤ ይህን ሥራ የጀመሩ ሰዎች ሁልጊዜም ስለልብ ሲነሳ የንግግራችን መነሻና መጨረሻ ሊሆኑ ይገባል በማለት አቶ ዮሐንስ አስገንዝበዋል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ይሄንን እገዛ ያደረገው የችግሩን ውስብስብነት፣ ትልቅነት የዛሬ ዓመት ባደረገው ጉብኝት ተገንዝቦ ነው። ይህን ያህል ገንዘብ ወጥቶባቸው አሁን ለማዕከሉ የቀረቡት ድጋፎች ለ250 ሕፃናት ሕክምና ብቻ ሊውሉ እንደሚችሉ እንደተነገራቸው አቶ ዮሐንስ አስታውቀዋል።

እንደሳቸው ገለጻ፤ የልብ ሕሙማን ሕፃናት መርጃ ማዕከሉን የመደገፉ ተግባር ዘላቂ መፍትሔ ያስፈልገዋል። አሰራሩን መቀየር በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ከማዕከሉ ቦርድ ጋር ውይይት ተደርጓል፤ የማዕከሉ የቢዝነስ ሞዴል ዘላቂ በሚሆንበት እና ራሱን በሚያግዝበት ደረጃ ለማድረስ ማሰብ የሚገባ መሆኑን ባንኩ ከማዕከሉ ኃላፊዎች ተነጋግሯል። ለዚህም የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እገዛ ለማድረግ ቃል ገብቷል።

ማዕከሉ በአንድ ዓመት እስከ ሁለት ሺህ ለሚደርሱ ሕፃናት አገልግሎት መስጠት እንደሚችል መስማታቸውን የገለጹት ዶክተር ዮሐንስ፣ እዚህ ደረጃ ለመድረስ ቁሳቁሱን ለማዕከሉ በቀላሉ ማቅረብ ይገባል፤ ለእዚህ ደግሞ ቁሳቁሱን በሀገር ውስጥ ማምረት መቻል አለብን ብለዋል። ይህን ለማድረግ ቴክኖሎጂው እንዳለና አዲስ ፈጠራ ውስጥ መግባት እንደማይጠይቅ ጠቅሰው፤ ይህን ፋብሪካ ከውጭ በማስመጣት መሥራት የሚቻልባት ሁኔታ እንዳለም አመላክተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ለሕክምና አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ቁሳቁስን በስፋት ማምረት የሚቻልባቸው ሁኔታዎች መመቻቸት ይኖርባቸዋል። የሕክምና ቁሳቁሱ አምራቾችም ወደዚህ ዘርፍ መምጣት ይጠበቅባቸዋል። የኢትዮጵያ ልማት ባንክም እነዚህን አምራቾች ለማገዝ ዝግጁ ነው። ባንኩ ለአጭር ጊዜ ድጋፎች በፍጥነት በመድረስ፤ በረጅም ጊዜ ደግሞ በኢንቨስትመንቱ እና እቅዱን በቴክኒክ በማገዙም ጭምር እገዛውን አጠናክሮ ይቀጥላል። የዚህ ዓይነት ድጋፎች ቀጣይነት ሊኖራቸው ይገባል።

በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ሆስፒታሉን በማሳደግ እንዲሁም የቢዝነስ ተቋም እንዲሆን በማድረግ በኩል አቅዱ ተዘጋጅቶ እንዲመጣ ከቦርድ ጋር ተነጋግረናል ሲሉም ዶክተር ዮሐንስ ገልጸዋል። በዚህ በኩል በእነሱ የሚሰራ ይኖራል ብለን እናስባለን፤ ያ እንዳለ ሆኖ ይሄ ጉዳይ እገዛ እንደሚያስፈልገው ይታወቃል ያሉት አቶ ዮሐንስ፤ ‹‹ እርግጠኛ ነኝ ዛሬ ወረፋ እየጠበቁ ያሉ ታማሚ ሕጻናት በርካታ ናቸው፤ ባንኩ አምና በገባው ቃል መሠረትም ለእዚህ ዓመትም ይህንኑ ለማድረግ ቃል ይገባል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የብራንድ አምባሳደር እና የኢትዮጵያ ልብ ሕሙማን ሕፃናት መርጃ ማዕከል የበጎ ፈቃድ አምባሳደር አርቲስት መሠረት መብራቴ በበኩሏ፣ በጎ አድራጊ ተቋማት እና ግለሰቦች የሕጻናትን ልብ በመጠገን እያደረጉ ለሚገኙት ተግባር አመስግናለች።

የዛሬ ዓመት አካባቢ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው ከባልደረቦቻቸው ጋር በማዕከሉ ተገኝተው ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት ከማዕከሉ የቦርድ አባላት እና አስተዳደር ጋር መወያየታቸውን አስታውሳለች።

የብራንድና የበጎ ፈቃድ አምባሳደሯ አርቲስት መሠረት እንዳለችው፤ ማዕከሉ ብቁ ባለሙያዎች እያሉት ከአቅም በታች እየሰራ ይገኛል፤ የዚህ ምክንያቱ ደግሞ የሕክምና ግብዓት እጥረት ነው። በግብዓት እጥረቱ ሳቢያ ብዙ ሕፃናት ለወረፋና ለእንግልት መዳረጋቸው ግንዛቤ ተወስዶበት በጉብኝቱ ወቅት ውይይት ተደርጓል።

የባንኩ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዮሐንስም ይሄንን መነሻ አድርገው ለስድስት ወራት የሚሆን ድጋፍ ለማዕከሉ ለማድረግ እና በቀጣይነትም ከማዕከሉ ጋር አብሮ ለመሥራት ቃል በገቡት መሠረት ቃላቸው በተግባር ውሎ ዛሬ ከ31 ሚሊየን ብር በላይ የሚያወጡ የሕክምና ቁሳቁስ ድጋፍ በመደረጉ በኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን ሕፃናት መርጃ ማህበር እና በራሷ ስም ምስጋና አቅርባለች።

እርዳታውም የ250 ሕፃናትን ተስፋ የሚያለመልም፣ የብዙ ወላጆችንም እንባ የሚያብስ ተብሏል። “እንደ ኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን ሕጻናት መርጃ ማዕከል አንድ ሕፃንን ልብ መጠገን፣ ሀገርን ማዳንና መጠገን ነው ብለን እናምናለን” ያለችው አርቲስት መሠረት፣ ድጋፉ ትልቅ እፎይታን እንደሚሰጥም አስታውቃለች።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ኤልሲ በመክፈት ከውጭ ምንዛሪ ጋር በተያያዘ ያሉትን የማህበሩን ችግሮች ከመቅረፍ አኳያ ሰፊ ድጋፍ አድርጓል። በዚህም ሳይወሰን ይህን ድጋፍ ይዞ ማዕከሉ ድረስ መጥቷል፤ በዚህ ብቻ ሳይሆን ማህበሩን በቀጣይነት ለመደገፍ እቅድ እንዳለውም አረጋግጧል ስትል ገልጻለች።

ሰውን መሠረት ካደረገ እና ሰውን ካስቀደመ ባንክ ጋር በአምባሳደርነት ማገልገሏ ትልቅ ክብር እንደሚሰማትም ጠቅሳ፣ የዚህ ዓይነት ድጋፍ፣ ኃላፊነት እና ቁርጠኝነት መሰል ተቋማትም ምሳሌነቱን እንዲወስዱ አመላክታለች።

እሷ እንዳለችው፤ ድጋፉ ጥቂት እፎይታ ይሰጣል፤ ችግሩ ሰፊ እና አሁንም ድረስ ወረፋ የሚጠብቁ በርካታ የሚንገላቱ ሕፃናት ያሉበት ነው። ባለሙያዎች እያሉ ማዕከሉ እጅ አጥሮታል፤ ማገልገል መሥራት እንፈልጋለን የሚሉ በርካታ ባለሙያዎች አሉት።

ሁሉም ኢትዮጵያውያን ግለሰቦች እና ተቋማት ለደጋፊው ጥቂት፣ ለሚደገፈው ሰው ግን ትልቅ ዋጋ ያለውን ድጋፍ በማበርከት የነገ ሀገር ተረካቢ ሕፃናትን ተስፋ እንዲያለመልሙም አርቲስቷ ጥሪ አቅርባለች። ጉዳዩ ሁሉም ዘንድ መድረስ አለበት፤ የሕፃናትን ልብ መጠገን የጋራ ሥራችን ነው፤ አብረን ተጋግዘን የሕፃናቱን ታሪክ እንቀይር በማለት ሃሳቧን ቋጭታለች።

ልማት ባንክ ያደረገው እገዛ ዘረፈ ብዙ ፋይዳ አለው። የቁሳቁሱ መገኘት ከብዙ ዘርፍ አኳያ ትልቅ ድጋፍ ነው የሚሉት ማዕከሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ዶክተር ሜክሎን መንግስቱ ናቸው። ዶክተር ሜክሎን እንዳሉት እንደ አንደ የጤና ባለሙያና እንደ ማዕከሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ብዙ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ነው ሲሉ ገልጸው፣ ድጋፉን ላደረገው የኢትዮጵያ ልማት ባንክም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

የዛሬ ዓመት አካባቢ በማዕከሉ ጉብኝት ሲደረግ የማዕከሉን ችግሮች፣ በልብ ሕመም የሚሰቃዩ ሕጻናት የሚደርስባቸውን እንግልት፣ የሚያሳልፉትን አሳዛኝ ሕይወት ስናስረዳ ከልብ ተረድተው በዛሬዋ ቀን በቦታው ላይ ተገኝተው መረዳታቸውን በተግባር ሲያሳዩን ለእኛ ትልቅ ተስፋ ሆኗል ሲሉም ነው የተሰማቸውን ደስታ የገለጹት።

እሳቸው እንዳሉት፤ ባንኩ ባደረገው ድጋፍ ለማዕከሉ የቀረቡት የሕክምና ቁሳቁስ ቢያንስ የ250 ሕጻናት ታካሚዎችን የልብ ቀዶ ሕክምና በዋናነት ለመሥራት ያስችላል። የልብ ቀዶ ሕክምና በሚሰራ ጊዜ ልብ ይቆማል፤ እቃዎቹ የዚህን የልብና የሰንባን ሥራ ተክተው የሚሰሩ ናቸው። ቁሳቁሱ ለልብ ቀዶ ሕክምናው አንኳርና የጀርባ አጥንት የሆኑ አላቂ እቃዎች ናቸው።

‹‹ብዙ መድኃኒቶች በሀገራችን ልናገኝ የምንችልባቸው ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ፤ እነዚህ አላቂ የሕክምና እቃዎች ግን በሀገር ውስጥ የሚገኙ አይደለም።›› ያሉት ሜዲካል ዳይሬክተሩ፣ እቃዎቹን ለማግኘት ብዙ ችግሮች እንደሚገጥም ነው ያመለከቱት።

ይህ ድጋፍ እነዚህን ሁሉ እቃዎች ለማግኘት የሚፈጀውን ጊዜና ውጣ ውረድ አስቀርቷል፤ ወጪንም መቀነስ አስችሏል፤ ይህ ድጋፍ ትልቅ እፎይታ ሰጥቶናል በማለት፤ የማዕከሉ ታካሚዎች የነበሩ አሁን በማዕከሉ የሚሰሩ፣ ከማዕከሉ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸውና ለማዕከሉ ከልባቸው ቀን ተሌት የሚተጉ እንዳሉና ድጋፉ ከቁጥርም በላይ መሆኑን አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን መርጃ ማህበር የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ ዶክተር ምህረተአብ ኤርሚያስ እንደገለጹት ተቋሙ 70 በመቶ ሕጻናት የልብ ታማሚዎች የሕክምና አገልግሎት ይሰጣል። አሁን ላይም በጠቅላላ ከ20 ሺህ በላይ ሕጻናት ክትትል የተደረገላቸው የሚገኝ ሲሆን ስምንት ሺህ ያህል ሕጻናት የልብ ቀዶ ጥገና ለማድረግ ወረፋ እየተጠባበቁ ይገኛሉ።

ማህበሩ አገልግሎቱን በክልሎች ከማስፋት በተጨማሪም ጅግጂጋ ሀዋሳ በመሳሰሉት በሆስፒታሎች የክትትል አገልግሎት እንዲያገኙ እየተደረገ መሆኑንም ጠቁመዋል። በማህበሩ በአንድ ጊዜ የልብ ቀዶ ሕክምና መስጠት የሚችሉ ሁለት ሐኪሞች ቢኖሩም ሁለቱንም በአንዴ የሚያሰራ የሕክምና ግብዓት የለም። አሁን ያለውን ባለሙያ በመጠቀም በዓመት 1500 ሕጻናት ቀዶ ጥገና ማድረግ ቢቻልም በግብዓት እጥረት በዓመት አንድ ሶስተኛ ያህሉ ብቻ እየተሰራ ነው ብለዋል።

ማህበሩ ላለፉት 35 ዓመታት የልብ ሕሙማን ሕጻናት የክትትልና ቀዶ ጥገና ሕክምና እየሰጠ የሚገኝ መሆኑ ይታወቃል።

# ወጣቶች

# «በምግብ እራስን ለመቻል የእንሰት ምርት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው»

## ወጣት እሱባለው አለልኝ

ክብረአብ በላቸው

ቴክኖሎጂና አዲስ የፈጠራ ሥራ የሰው ልጆችን ሕይወት በብዙ አሻሽሏል፡፡ ከትምህርት፣ ከጤና፣ ከግብርና እና ከሌሎች ዘርፎች አንፃርም የሚሰጠውን ጠቀሜታና የአጠቃቀም ሂደቱን ብንመለከት እንደ ዘርፎቹ ዓይነት ጥቅም ላይ የሚውልበት መንገድም ይለያያል። የሚጠቀምባቸው መሳሪያዎችም እንዲሁ እንደ አገልግሎቱ ዓይነትና ስፋት ይለያያሉ፡፡ እንደ ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ለሚገኙ ሀገራት ደግሞ የቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራ ፋይዳው የላቀ ነው። በተለያዩ ዘርፎች ላይ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የማደግ ዕድል እንዳላት ሀገር፣ የማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ ለመሻሻል፣ ለትምህርት ለግብርናና ለጤና አገልግሎት፣ በአጠቃላይ በሁሉም ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን በቴክኖሎጂና በአዲስ የፈጠራ ሥራ መታገዝ የግድ ነው።

በምግብ እራስን ችሎ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የማገዝ ጉዳይ ከልማዳዊ አሠራር ሥርዓት ማላቀቅ መቻል እንዳለበት ብዙዎች ይስማማሉ። በፍላጎትና በአቅርቦት መካከል ያለውን የሚዛን መዛባት ለማረም ኋላቀር አሠራሮችን በመፈተሽ ዘርፉን የማዘመን እስትራቴጂካዊ አሰራሮች ላይ ልዩ ትኩረት ያስፈልጋል፡፡ በግብርና ዘርፉ በተጨማሪነት ጥንቃቄ መደረግ ያለበት በንግድ ሰንሰለቱ ውስጥ ያሉ ተዋንያንን የሚያውኩ ሕገ ወጥ ድርጊቶች ምንጫቸው መፈተሽ ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም የገበያ ሥርዓቱ የሚያውኩና ከአርሶ አደሩ ማሳ እስከ ገበያ ድረስ ባለው መካከል ያለው በቀላል ቁጥር የማይገለጽ ሕገ ወጥ ደላላ አደብ እንዲገዛ ሥርዓት መበጀት ይኖርበታል። ሰፊ ለም መሬት፣ ከፍተኛ መጠን ያለው የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውኃ፣ ተስማሚ የአየር ፀባዮች፣ እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ ወጣት የሰው ኃይል ባለበት ሀገር ውስጥ በምግብ ዕጦት መቸገር መብቃት ያለበት ጉዳይ እንደሆነ እሙን ነው።

በእንስሳት ሀብትም ቢሆን ከአፍሪካ አንደኛ ደረጃን ይዘን ሥጋ፣ ዶሮ፣ ቅቤ፣ ወተት፣ ዕንቁላል እና ሌሎቹ የእንስሳት ተዋጽኦ የቅንጦት ምግብ መሆን እንቆቅልሽ ያደረገው የአሰራር ሥርዓት በየደረጃው ተፈትሾ መስተካከል ያለበት ነው፡፡ የትኛውም አደጉ፣ በለጸጉ የምንላቸው ሀብታም ሀገራት የመጀመሪያው መሸጋገሪያ ድልድያቸው የግብርና ዘርፉን በሚያስፈልገው ሁሉ በማዘመን ነውና እንደ ሀገር በዘርፉ መከወን ያለባቸውና እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎች ከንግግር ባለፈ የሀገራችንን ኢኮኖሚ አቅምን በሚያረጋግጥ እና በሚያረጋጋ ሁኔታ መሥራት ከሁሉም የሚጠበቅ ስለመሆኑ አያጠራጥርም።

ወጣት እሱባለው አለልኝ ይባላል ውልደቱ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ ዞን ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በወላይታ ሶዶ ሊጋባ ትምህርት ቤት ነው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ በዛው ከተማ በሚገኝ የወላይታ ሶዶ መሰናዶ ትምህርት ቤት ተከታትሏል። ከዛ በመቀጠል በ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ጥሩ ውጤት በመምጣት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቱን ለመከታተል ወደ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ማቅናት ችሏል።

በትምህርት አቀባበሉ በመካከለኛ ደረጃ ከሚመደቡ ተማሪዎች መካከል እንደነበር የሚናገረው ወጣት እሱባለው በ2008 ወደ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲን ሲቀላቀል ለመማር አቅዶ የነበረው የሕክምና ትምህርት ነበር። ቢሆንም ይህ ባለመሳካቱ በሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቆይተው ለኬሚስትርና ባዮሎጂ ትምህርቶች ልዩ ፍቅር ስለነበረው ከነዚህ ትምህርቶች ጋር ይበልጥ ቁርኝት አለው ያለውን የኬሚካል ምህንድስና ትምህርት በመምረጥ መከታተል ችሏል።

በ2013ዓ.ም የኬሚካል ምህንድስና ትምህርቱን አጠናቆ የተመረቀው ወጣት እሱባለው በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ስለነበረ ቆይታ ሲናገር፤ ከምህንድስና ትምህርቱ ባሻገር የቢዝነስ ማኔጅመንት ትምህርት በመከታተል በሁለት የትምህርት ዓይነት ስኬታማ መሆን ቻለ። በመሆኑ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የነበረው ቆይታ ያልበከናና መጨረሻውም በውጤት የተደመደመ እንደሆነ በደስታ ይናገራል።

ከልጅነቱ ጀምሮ ለአዳዲስ ነገሮች ግኝት፣ ለፈጠራ ቀልቡ ይሳብ እንደነበር የሚናገረው ወጣት እሱባለው፤ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በነበረው ቆይታ ከትምህርቱ ጎን ለጎን የተለያዩ ተቋማትና ግለሰቦች ስለፈጠራና መሰል ጉዳዮች የሚሰጡትን ስልጠና ለመውሰድ ጥረት ያደርግ እንደነበር



ያስታውሳል።

ተቀጥሮ በአንድ የመንግሥት ወይም የግል ድርጅት ውስጥ በመሥራት ውጤታማ እሆናለሁ የሚል እምነት ያልነበረው እሱባለው ተቀጥሮ መሥራት ምርጫው ባለመሆኑና አዲስ አሠራር መገንባት ከጠንካራ ሠራተኝነት hard work ባሻገር ጥበበኛ ሠራተኛ smart worker መሆን የሚፈልግ በመሆኑ በራሱ መንገድ ተጉዞ ውጤታማ ለመሆን ጥረት ስለማድረጉ ያስረዳል።

በአሁኑ ሰዓት Bright Enset starch manufacturing የሚል ስያሜ የተሰጠው ኩባንያ መስርቶ በተለይ በእንሰት ተክል ላይ የምርምር ሥራ በስፋት እያከናወነ የሚገኘው ወጣት እሱባለው እያከናወነ ስላለው አዲስ የፈጠራ ሥራ ሲናገር፤ ባደገበት አካባቢ የእንሰት ምርትና ብሎም የንጥረ ነገሩ ጠቃሚነት በአግባቡ የሚረዳው በመሆኑ ይህ ተክል በመላው የሀገሪቱ ክፍል ተስፋፍቶ ለምግብነት የማዋል ትልም ስላለው እንሰትን በተሻለ ጥረትና ምርት ዘርፈ ብዙ ጥቅም ሊሰጥ በሚችል መልኩ አምርቶ ለገበያ ለማቅረብ የምርምር ሥራውን ስለመጀመሩ ይናገራል።

የእንሰት ምርት በተፈጥሮ ድርቅን መቋቋም የሚችል ቢሆንም ኢትዮጵያ በተገቢው መልኩ እየተጠቀመችበት አይደለም የሚለው እሱባለው፤ ቴክኖሎጂ በመፍጠር ምርቱን ለማሳደግ አልተቻለም በደቡብ የሀገሪቱ ክፍል በስፋት የሚመረተውን የእንሰት ምርት በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢ እንዲመረት ለማድረግ ባለመታደሉ ይህንን ችግር እንዴት መፍታት ይቻላል በሚል በዘርፉ ምርምር ለማድረግ እንደተነሳ ይናገራል።

እንሰት በመሐል እና በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ማህበረሰብ ዘንድ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጥቂቱ እየታወቀ ቢመጣም አዘገጃጀቱ አድካሚ በመሆኑ እርሱ ይህንን በመቅረፍ በዘመናዊ መንገድ በቀላሉ አዘጋጅቶ ለገበያ እንደቀረበ በተጨማሪ የእንሰት ዱቄቱ በተለየ መልኩ ለሁሉም ዓይነት የምግብ ስልቶች የሚውል ምንም ዓይነት ሽታ የሌለው በመሆኑ ወደፊት ባሉት ጊዜያት በስፋት ተመርቶ ለገበያ ቀርቦ ተወዳጅነት የሚያተርፍ ስለመሆኑ የማያጠያይቅ እንደሆነ ይገልጻል።

ኢትዮጵያ በዓመት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማውጣት 20ሺህ ቶን ለምግብ ፍጆታ የሚውል starch ኢምፖርት ታደርጋለች ይህንን የሚያስቀር ዱቄት የእንሰት ቡላ በመጠቀም ለኬክ፣ ለኩኪስ፣ ለዳቦ መጋገሪያ መሆን የሚችል ዱቄት መምራት እንደቻለ የሚናገረው ወጣት እሱባለው፤ በተለምዶ ጥቅም ላይ ከሚውለው ዱቄት በተሻለ የከርቦሀይድሬት መጠን ስላለውና ካለምንም የኬሚካል ንኪኪ ነፃ ስለሆነም ጤናማ በመሆኑ ተመራጭነቱ የማያጠያይቅ እንደሆነ ይናገራል።

በአሁኑ ሰዓት ገበሬው እንሰት ከማሳው እየነቀለ ቡናና ባህር ዛፍ ነው እየተከለ ያለው የሚለው የፈጠራ ባለሙያው ወጣት እሱባለው፤ የዚህ ምክንያትም እንሰት ምንም ዓይነት ገቢ እያስገኘለት ባለመሆኑ ነው። እንሰት ድርቅ የመቋቋም አቅሙ ከፍተኛ ነው። በአዲሱ የምርምር ሥራም እንሰት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ተለምዶ ዘመናዊ በሆነ መንገድ ምርት እንዲሰጥ ለማድረግ በተለያዩ አካላት ትኩረት ተሰጥቶ ቢሰራ መልካም እንደሆነ ይናገራል።

ሀገሪቱ በብዙ መመዘኛ አንፃር ጥቅሙ ብዙ ለሆነው የእንሰት ልማት ከስንዴ ልማት ያልተናነሰ ትኩረት መስጠት አለበት የሚለው ወጣቱ፤ በተለይ በደቡብ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዘንድ ከምግብና ባለፈ ለብዙ ነገር ጥቅም ላይ የሚውለው የእንሰት ተክል ያለው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ በአግባቡ ተውቆ ማህበረሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ምርታማነቱን በማስፋት የሚሰራው የምርምር ሥራ በመንግሥት ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ እንደሆነ ያነሳል።

እርሱ በሚሰራው የምርምር ሥራ የቆጮ ምርቱ ላይ የሚኖረው ምንም ዓይነት ጉዳት እንደሌለው የሚናገረው እሱባለው፤ በእርሱ የፈጠራ ሥራ ቆጮው እንዳለ ሆኖ ዱቄቱን ለማምራት የሚጠቀሙ የቡላውን ምርት ብቻ በመጠቀም በመሆኑ የሚሰራው የምርት ብክነት በከፍተኛ ደረጃ የሚቀንስ እንደሆነ ይናገራል።

የምርምር ሥራው ውጤታማነት ጥያቄ የሚነሳበት እንዳልሆነ የሚናገረው ወጣቱ፤ 20 ኪሎ ግራም የሚሆን በኢትዮጵያ የተመረተ ዱቄት ከእንሰት በኤክስፖርት ደረጃ በማምራት ለናሙና ወደ ውጭ በመላክ መረጋገጥ እንደተቻለ አዋጭነቱም ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የሚያጠራጥር አይደለም አርሶ አደሩም የቆጮ ምርቱን ለራሱ እየተጠቀመ ለእነርሱ የቡላ ምርት በሽያጭ እያቀረበ ከዚህ በፊት ባልተለመደ መልኩ ተጨማሪ ገቢ ማግኘት የሚችልበት ዕድል እንዳመጣለት ያስረዳል።

መንግሥት ለአረንጓዴ ልማት የሰጠውን ትኩረት በእንሰት ተክል ላይም መስጠት አለበት የሚለው ወጣት እሱባለው፤ የተጀመረው የፈጠራ ሥራ ተስፋፍቶ በመላው ኢትዮጵያ እንሰት ለምግብነት እንዲውል ለማድረግ በቴክኖሎጂና ምርምር የተደገፈ የግብርና እስትራቴጂ ነድፎ መንቀሳቀስ እንዳለበት ይናገራል።

በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት በተዘጋጀው የክረምት ወራት የቴክኖሎጂ ማበልጸጊያ ፕሮግራም ላይ ተሳትፎ የነበረው የፈጠራ ባለሙያው በዚያ ስለነበረው ቆይታ ሲናገር፤ ብዙ እውቀት ያገኘበት፣ ከተለያየ አካባቢ ከመጡ የፈጠራ ባለሙያዎች ጋር እርስ በእርስ በሚኖር ግንኙነት የተለያየ ልምድ የቀሰመበት፣ የፋይናንስ ድጋፍ መገኘት እንዲችል ከባንክ ጋር ትስስር መፍጠር የሚቻልበት መንገድ የተገኘበት በመሆን የክረምት ቆይታው የተዋጣለት እንደሆነ ይናገራል።

እንደ ሀገር በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ያሉ ወጣቶች በአንድ ቦታ ተሰባስበው እርስ በእርስ በሚኖራቸው ግንኙነት በተናጥል ከመሆን በጋራ ትልቅ ነገር ማለም እንዲችሉ ለማድረግ የተሰራው ሥራ ይበል የሚያሰኝ ነው። ጅምር የፈጠራ ሥራ ባለቤቶች ያለባቸው ችግር ምንድነው በማለት ወጣቶችን ከተለያየ አካባቢ ምግብ፣ ማደሪያ፣ ተችሎ ማሰልጠን ያልነበረ ነው። ይህንን ትልቅ ዕድል ላመቻቸው ተቋም ያለው ምስጋና ትልቅ እንደሆነ ወጣቱ ተናግሮ፤ የጎደለ ነገር ለማሟላት ከዚህ በፊት ባልተለመደ መልኩ የተደረገው ጥረት መበረታታት የሚገባው እንደሆነና ለብዙዎች ተስፋ ሰጪ ጅምር በመሆን ቀጣይናት ባለው መልኩ መሠራት ያለበት እንደሆነ ያስረዳል።

ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ የተለያዩ ድርጅቶች የምርምር ሥራውን በሚሰራበት ወቅት ድጋፍ እንዳደረጉለት የሚናገረው እሱባለው፤ መንግሥት በየአካባቢው እንደ እርሱ ዓይነት የፈጠራ ዝንባሌ ያላቸው ወጣቶች ሥራቸውን ማጎልበትና ማሳደግ የሚችሉባቸውን የፈጠራና የቴክኖሎጂ ማዕከላት ቢስፋፉ የተሻለ ሥራ መሥራት እንደሚቻል እና የቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራ በይበልጥ ድጋፍና ክትትል የሚያገኝበት መንገድ ቢኖር መልካም ነው ይላል፡፡

የፈጠራ ሥራውን ለመሥራት ጥረት በሚያደርግበት ወቅት የተለያዩ ተግዳሮቶች እንደነበሩ የሚናገረው ወጣት እሱባለው ከግለሰቦች የሚሰጡ አሉታዊ አስተያየቶች ነበሩ ነገር ግን የታየውን ህልም የሚሉ ሰዎች ነበሩ እርሱ ግን ያንን ፋይዳ አልባ አስተያየት ለመስማት ጆሮ እንዳልሰጠ ይናገራል።

የወደፊት ህልሙ ምን እንደሆነ ወጣቱ ሲናገር፤ የእንሰት ምርትን ለዓለም ለማስተዋወቅ ሲሆን በቡና፣ በአበባ ምርት በመላው ዓለም የምትታወቀው ኢትዮጵያን በእንሰት ማስተዋወቅ ይፈልጋል። እንሰት ደግሞ የኢትዮጵያ ሀገር በቀል ምርት እንደመሆኑ ይህንን ለዓለም በማስተዋወቅ ምግብነቱ ዕውቅና እንዲኖረው የማድረግ ግብ እንዳለው ተናግሯል። እንሰት ከኢትዮጵያ ባለፈ በድርቅና በምግብ ዕጥረት ለሚሰቃዩ የአፍሪካ ሀገራት ሕዝቦች ለምግብነት እንዲውል የማድረግ ህልም እንዳለው ተናግሯል።

ወጣት እሱባለው ለወጣቶች ባስተላለፈው መልዕክት አንድ ነገር ለማድረግ ሲታሰብ ሁልጊዜ ዋጋ መክፈል ይኖረዋል፤ ፅንቶና ተግቶ በመሥራት የማይሳካ ነገር ግን እንደሌለ ተናግሯል። የኢትዮጵያን ነገ የለመለመ የማድረግ ኃላፊነትና ግዴታ ያለባቸው የዛሬው ትውልድ ወጣቶች በመሆናቸው ለዓላማቸው መሳካት መክፈል ያለባቸውን መስዋዕትነት ሁሉ መክፈል አለባቸው። የነገው ራዕያቸውን ከግብ ለማድረስ ቀን ሌሊት ሳይሉ እና ተስፋ ሳይቆርጡ መትጋት እንደሚገባቸው አስረድቷል።

# የምድር በረከት

## አምራቹን ከገዢው፤ ከልምድና ከቴክኖሎጂ ያገናኘው ኤክስፖ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**



የማዕድን ሀብትን ለማልማት ወሳኝ ከሆኑት መካከል የዘርፉ ኢንቨስትመንት ይጠቀሳል። የማዕድን ዘርፉን ኢንቨስትመንት ለመሳብ ከሚያስችሉ ሥራዎች መካከል ደግሞ ኤክስፖ አንዱ እንደሆነ ይታመናል። ኢትዮጵያም ይህንን የማዕድን ሀብትንና የማዕድን ዘርፉን ለማልማት የተዘጋጁ ምቹ ሁኔታዎችን የሚያስተዋውቀውን፣ የማዕድን ዘርፉን ተዋንያን በአንድ የሚያገናኘውን፣ የዘርፉን የውጭ ኢንቨስትመንት መሳብ የሚያስችለውን ኤክስፖ በማዘጋጀት ከዘርፉ የበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን እየሰራች ትገኛለች።

ባለፈው ዓመት የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ ማካሄዷ ይታወሳል። ዘንድሮም ካለፈው ዓርብ ጀምሮ ለአምስት ተከታታይ ቀናት ሁለተኛውን ኤክስፖ በሚሊኒየም አዳራሽ አካሂዳለች። የዘንድሮው ኤክስፖ ከአምናው በብዙ መልኩ የተለየ ነው። ባለፈው ዓመት ለሶስት ቀናት ብቻ የተካሄደ ሲሆን ዘንድሮ ለአምስት ቀናት ነው የተካሄደው። ዘንድሮ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የመወያያ ጽሑፎች ቀርበው ውይይቶች ተካሂደዋል።

ኤክስፖው ለሀገሪቱ፣ በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት ትልቅ አቅም መፍጠሩ ተጠቁሟል። የሀገሪቱን የማዕድን ሀብት ዜጎች በጋራ ተቀናጅተው አክሲዮን እየመሰረቱ ጭምር እንዲያለሙም ጥሪ ቀርቦበታል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ኤክስፖው በተከፈተበት ወቅት እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ በማዕድን ሀብት የታደለች ሀገር ናት፤ ይህን የማዕድን ሀብት በሚፈለገው ደረጃ አልምቶ በመጠቀም ለተተኪው ትውልድ የተሻለች ኢትዮጵያን ማስረከብ ይቻላል።

‹‹በሀገሪቱ በሁሉም አካባቢዎች አስደናቂ የማዕድን ሀብቶች አሉ›› ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ‹‹ይህን የማዕድን ሀብት በአግባቡ ማወቅና መጠቀም ከቻልን ለሀገሪቱ የብልጽግና ጉዞ መሠረት እንጥላለን። ለዚህ ደግሞ መንግሥት ለሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ትኩረት ከሰጣቸው አምስት ዘርፎች አንዱ የማዕድን ዘርፍን አድርጎታል።›› ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ‹‹ባለፉት ጥቂት ዓመታት የማዕድን ሀብት አለን የለንም የሚለውን ለማወቅና ለመረዳት ጥረት ስናደርግ ቆይተናል። አሁን ደግሞ ያሉትን የማዕድን ሀብቶች አውቀን ባንጨርስም ኢትዮጵያ በርካታ የማዕድን ሀብት የታደለች ሀገር መሆኗን መረዳት ችለናል›› ሲሉ ጠቅሰው፣ ከውጭ ሀገር የሚገቡ የማዕድን ምርቶችን በሀገር ውስጥ በመተካት የውጭ ምንዛሬን በማዳንና የተለያዩ ማዕድናትን ወደ ውጭ በመላክ በርካታ የውጭ ምንዛሬን በማስገኘት ለኢኮኖሚያዊ እድገት አይተኪ ሚና መጫወት እንደሚገባ አስገንዝበዋል። በማዕድን ሀብቱ ይህን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ሥራ እየተሰራ መሆኑንም ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የወርቅ፣ የከበሩ ድንጋዩችና የበርካታ ውድ ማዕድናት መገኛ እንደሆነች ኤክስፖውም ማመላከቱን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ተማሪዎች፣ ተመራማሪዎች፣ ነጋዴዎች፣ ኢንቨስተሮችና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት በዘርፉ ምን እንዳለና ምን እየተሰራ እንደሆነ በመረዳት ኢኮኖሚውን ሊደግፉ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ መሥራት እንደሚገባቸውም አስገንዝበዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደተናገሩት፤ ኤክስፖው ኢትዮጵያ ያላትን የማዕድን ክምችት የሚያሳይ፣ የማዕድን ሀብትን ወደ ውጭ ለመላክ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር እና ለሚቀጥለው የብልጽግና ጉዞ መሠረት የሚጥል ዘርፍ መሆኑን መረዳት የሚቻልበት ነው። የማዕድን አምራቾች፣ ላኪዎች፣ ተጠቃሚዎች፣ የቴክኖሎጂ አምራችና አቅራቢዎች ተገናኝተው ምርትና አገልግሎታቸውን የሚያስተዋውቁበት እና ትስስር የሚፈጥሩበት ነው።

ስለዚህም የምናስበው የእድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ የኢትዮጵያ የግል ዘርፍ በግል ማምረትና ኢንቨስት ማድረጉን አቁሞ በጋራ መሥራት የምንችልበትን፣ እውቀት የምናሰባስብበትንና የምንበለጽግበትን መንገድ መፍጠር ይገባል ሲሉም አስገንዝበዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከችግር ነጻ የሆነ የመልሚያ መንገድ እንደሌለም ጠቅሰው፣ በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጋራ በመፍታት ወደ ብልጽግና ከፍታ መገስገስ እና ለተተኪው ትውልድ የተሻለች ኢትዮጵያን ማስረከብ እንደሚገባም አመልክተዋል።

የማዕድን ሚኒስትሩ ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ይህ ኤክስፖ በርካታ እድሎችን ለሀገሪቱ ዜጎች የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ በሀገሪቱ በሁሉም አካባቢዎች የሚገኙት የማዕድን ሀብቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያስችላል። በተጨማሪም መንግሥት ባለሀብቶች ከባለሀብቶች ጋር እንዲቀራረቡ ከፍተኛ እድል የሚፈጥርበትም ነው።

ኤክስፖው ኢትዮጵያ ያላትን የማዕድን ሀብት ለማስተዋወቅ ፋይዳው ወሳኝ መሆኑንም አመልክተዋል። በዚህ በኩል ባለሀብቶች እና በዘርፉ የተሰማራው የግል ዘርፍም ድርሻቸው የጎላ መሆኑን አመልክተው፣ ባለሀብቶች ያለውን ሀብት ተመልክተው ወደ ሥራ እንዲገቡ ያስችላቸዋል ብለዋል።

ማዕድኑን በሚፈለገው ደረጃ አልምተን ተጠቃሚ መሆን ካልቻልን የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት ጥያቄ ውስጥ ይገባል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ለዚህም የሚያግዝ፤ በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ይፈታል ተብሎ የታመነበት ብሔራዊ የማዕድን ካውንስል መቋቋሙንም አስታውቀዋል። ባለድርሻ አካላት በጋራ የዘርፉን ችግሮች ለመፍታት እንዲረባረቡ ጥሪ አቅርበዋል።

ከ90 በላይ ኩባንያዎች በተሳተፉበት በዚህ ኤክስፖ የወርቅ፣ የድንጋይ ከሰል፣ ለጌጣጌጥ የሚውሉ የከበሩ ማዕድናት እንዲሁም የኢንዱስትሪ ማዕድናት፤ ቴክኖሎጂ፤ ሲሚንቶና ብረት ይዘው የቀረቡ መሆናቸውን የጠቀሱት ኢንጂነር ሀብታሙ፤ ኤክስፖው ከዚህም ባሻገር በኮንፈረስ የታጀበና ብዙ እውቀትን ያስጨበጠ መሆኑን አስታውቀዋል።

ኤክስፖውን በብዙ ነገሩ ልዩ ነው ሲሉ ገልጸውታል። በዘርፉ ልምድና ተሞክሮዎች ያሏቸው ሀገራት ልምዳቸውን ያጋሩበት፣ በተመሳሳይ የሀገሪቱ ማዕድናት ምን እንደሚመስሉ፤ የት እንደሚገኙና በምን መልኩ መልማት እንዳለባቸው ያመላከቱ ጥናቶች የቀረቡበት መሆኑን ልዩ ከሚያደርጉት ምክንያቶች ናቸው ሲሉ ገልጸዋል። ይህ ደግሞ ለአምራቾች፣ ለባለሀብቶች፣ ለመንግሥትም የቀጣይ አቅጣጫ ጠቋሚ መሆኑን ተናግረዋል። ለተማሪዎችና ለተመራማሪዎችም የዘርፉ እውቀት የት እንዳለ እንዲረዱ ያስቻለ መሆኑን ጠቅሰው፣ የውጭ ኢንቨስተሮች ጭምር በየትኛው ላይ፣ የት ቦታ ሄደው ማልማት እንደሚችሉ ምልክት የሰጠ መሆኑንም አመልክተዋል።

ከኤክስፖው ጎን ለጎን ሶስት ሲምፖዚየሞች ተካሂደው ውይይቶች ተደርገዋል። በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የጂኦሎጂ መምህር ተባባሪ ፕሮፌሰር ታረቀኝ ታደሰ በኤክስፖው ላይ ጥናታዊ ጽሑፍ ካቀረቡት መካከል አንዱ ናቸው። እሳቸውም ከማዕድን ዘርፍ ተገቢውን ጥቅም ለማግኘት አንድ አካልን ብቻ መጠበቅ አይገባም፤ ሁሉም የየራሱ ድርሻ አለው ሲሉ ይገልጻሉ።

በማዕድን ጉዳይ ከግለሰብ እስከ ማህበረሰብ ድረስ ተባብሮ መሥራት እንደሚገባው ያስገነዝባሉ። ለዚህም ምክንያቱ ሀብቱ የጋራ መሆኑን፤ ተጠቃሚነቱም ሆነ ጉዳቱ እንደዚያው የጋራ መሆኑን ያመለክታሉ። ‹‹ለሥራ ሁሉ ርብርብ ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ በርካታ የማዕድን ሀብት ባለቤት እንደሆነች መናገር ብቻ በቂ አይደለም። ከዚያ ተሻግሮ ማልማቱ ላይ ተጋግዞ መሥራት ይገባል›› ሲሉ ያስገነዝባሉ።

ተባባሪ ፕሮፌሰር ታረቀኝ እንዳሉት፤ የማዕድን ዘርፍን የማልማት ሥራ በርግጥ ብዙ ሀብት፤ በዘርፉ የተማረ የሰው ኃይልን፣ ቴክኖሎጂዎችን ይጠይቃል። በዚህ በኩል ደግሞ መንግሥት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይኖርበታል።

ቴክኖሎጂ ማስፋፋትና ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ፈሰስ ማድረግ ከምንም በላይ ያስፈልጋል። መንግሥት በዚህ በኩል ቁርጠኛ መሆኑን እየገለጸ ይገኛል፤ በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ይህን እድል መጠቀም ይኖርባቸዋል። ለዚህ ደግሞ እንደነዚህ ዓይነት ኤክስፖዎችን ወደተግባር በመቀየሩ በኩል ትኩረት ከተደረገ መልካም እድል ይዘው ይመጣሉ። ስለዚህም ሁሉም ቃል የተገባውን ወደ ሥራ ይቀይረውና ማዕድኑን ለሀገራችን እድገት እናውለው ሲሉ ይመክራሉ።

ወይዘሮ ኤልሳቤጥ ወርቁ በኤክስፖው ተሳታፊ ከነበሩ መካከል ናቸው። ሮማርብል ኤንድ ግራናይት ትሬዲንግ የተባል ድርጅት አቋቁመው በአምራችነትና አከፋፋይነት ይሰራሉ። ሀገሪቱ በርካታ የተፈጥሮ ማዕድን ሀብት ያላት ብትሆንም ይህንን ሀብት አልምቶ መጠቀም ላይ ብዙ ርቀት አለመጓዟን ከቀረቡት ኮንፍረንሶች መረዳት እንደቻሉ አስታውቀዋል። ዘርፉ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት መሠረት ሊጥል እንደሚችል ገልጸዋል። ዘርፉ በቀደሙ ጊዜያት ተገቢው ትኩረት ሳይሰጠው መቆየቱን መታዘባቸውን ጠቅሰው፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተከናወኑ ተግባራት ምን ዓይነት ለውጦች እየመጡ እንደሆነ የራሳቸውን ድርጅት በአብነት ጠቅሰዋል።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ ያላትን የማዕድን ሀብት መለየትና ሀብቱን ማስተዳደር የሚያስችል አቅም በመገንባት በኩል ውስንነቶች አሉባት። ለዚህም ማሳያው በርካታ የማዕድን ዓይነቶች ሀገር ውስጥ ቢኖሩም፣ ከውጭ ሀገር በማስመጣት ጥቅም ላይ ሲውል እየታየ ያለበት ሁኔታ ነው።

ይህ ደግሞ ሀገሪቱንም ሆነ ነጋዴውን ወይም አከፋፋዩን በብዙ መልኩ ይጎዳል። አንዱ የውጭ ምንዛሬ ጉዳይ ሲሆን፤ ኩባንያው እቃውን ለማምጣት ዶላር ሲጠይቅ በበቂ ሁኔታ እንዳያገኝ ያደርገዋል። ከዚያም በላይ ደግሞ ሀገሪቱ መጠቀም ያለባትን ያህል እንዳታገኝ ያስችላታል። የውጭ ምንዛሬውን መስጠት እንጂ መቀበል ላይ ብዙም ተጠቃሚ አትሆንም። የማዕድን ውጤቶች በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ቢሆንና አከፋፋዮች ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርቡት ማዕድን ቢኖራቸው ብዙ ነገሮች ይቀላሉ። የውጭ ምንዛሬ ማውጣቱ ይቀርና ማስገባቱ የተለመደ ይሆናል።

በአሁን ወቅት መንግሥት ለማዕድን ዘርፉ የሰጠው ትኩረት እነዚህንና መሰል ችግሮችን እንደሚፈቱ ያግዛል ያሉት ወይዘሮ ኤልሳቤጥ፣ ድርጅታቸው እምነበረድ፤ ግራናይትና ላይም ስቶንን በሀገር ውስጥ ሲያመርትና ሲያከፋፍል በብዙ መልኩ የውጭ ምንዛሬን አድኗል። በእንደነዚህ ዓይነት ኤክስፖዎች ደግሞ ኤክስፖርት ለማድረግ የሚያስችል ሥነ ምህዳርም መፍጠር ችለናል ሲሉ ይገልጻሉ። ምክንያቱም ኤክስፖው ከአስመጪና ላኪዎች፣ ከውጭ ኩባንያዎች እና በዘርፉ ከሚሰሩ አካላት ጋር አስተዋውቆናል ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ኤክስፖው ከሌሎች የሥራ ልምዶችን እንድንቀስም አስችሎናል ሲሉ ጠቅሰው፣ እኛ የሌሎንን የእምነበረድ አሠራሮች ከሌሎች እንድንቀስምና ልምድ እንድንለዋወጥ፤ ገዢ ደንበኞችንም እንድናፈራ አስችሎናል። ስለዚህም ኤክስፖው በብዙ መልኩ ለእኛ ልዩ ትርጉም አለው ሲሉም አመላክተዋል።

‹‹ሥራ ለእድገት ኦፓል አምራች ማህበር›› በሚል ድርጅት በኦፓል አምራችነት የተሰማሩት አቶ ማስሬ ሀሰን፣ መንግሥት የብዝሀ ኢኮኖሚ አተያይን ተግባራዊ በማድረጉ የማዕድን ዘርፍ አንዱ የኢኮኖሚ ምሰሶ ተደርጎ እንዲወሰድ አድርጓል ይላሉ። ይህ ደግሞ በተለይ በባህላዊ መልኩ የሚያመርተው ተደራጅቶ በዘመናዊው መንገድ ወይም በኢንዱስትሪ የሚያመርትበትን፤ በጥራት አምራች የሚሆንበትን እድል እየፈጠረ ነው ብለዋል።

መንግሥት ለዘርፉ በሰጠው ልዩ ትኩረት ከሀገሪቱ የማዕድን ሀብት ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ከዘርፉ ተዋናዮች ጋር በቅንጅት እየሰራ እንደሆነ ይሰማናል የሚሉት አቶ ማስሬ፣ በማህበር ተደራጅቶ መሥራትን ያወቅነውና ተጠቃሚ የሆነው በዚህ ምክንያት ነው ሲሉም ይገልጻሉ። የማዕድን ዘርፍ ከፍተኛ ቴክኖሎጂ እንደሚፈልግ ተናግረው፣ መንግሥት ከዚህ አኳያ ድጋፍ ሲያደርግ በተወሰነ መልኩ እያየን እንገኛለን፤ ድጋፉ እኛንም ቢያካትተን መልካም ነው ሲሉም ጠይቀዋል።

‹‹አሁን ባለንበት ደረጃ ብዙ ጉልበት እያፈሰስን ነው ማዕድኑን የምናወጣው። ከዚያ ይልቅ የምናመርትበትን ቴክኖሎጂ የምናገኝበት እድል ቢመቻች ብዙ ነገሮችን መቀነስ እንችላለን። ለአብነት በብዛትና በጥራት ማምረት፣ ለሀገር ውስጥ አከፋፋዮች በቀላል ዋጋ ማቅረብ እንድንችል ያግዘናል ብለዋል።

የማዕድን ሀብትን ጥቅም ላይ ለማዋል ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ የሚጠይቅና ረጅም ጊዜ የሚፈልግ እንደሆነ በትምህርት ከአገኘነው ልምድ እናውቃለን ያሉት አቶ ማስሬ፣ ይህ ካልተገኘ በዘርፉ እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድርም ጠቁመዋል። መንግሥት ብቻ ሳይሆን ባለሀብቶችም አቅማቸውን በማሰባሰብ በዘርፉ ኢንቨስት ቢያደርጉ፤ እንደ እኛ ዓይነት ማህበራትን ቢያግዙ፣ አልያም በጋራ የምንሰራበትን እድል ቢያመቻቹ መልካም ነው ብለዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## መልካም ነፍስ

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

‹ትቸር..! አለችው ከክፍል ወጥቶ ወደ ቢሮው ሲሄድ ከኋላው ተከትላ።

ለይኩን ወደ ኋላው ሲዞር ሳራን አጠገቡ አያት። ፊቱ መቆሟ አልገረመውም ሁሌ የሚያስገርመው ወደ እሱ ስትመጣ ብዙ አበሳን ነፍሷ ላይ ተሸክማ መሆኑ ነው። የነፍሷ አበሳ ይገርመዋል..እሱ ፊት እሷና ነፍሷ መከረኛ ናቸው..ለምን የሚለውን ጥያቄ ግን አልደረሰበትም።

‹እሺ ሳራ..ምን ልታዘዝ? ክፍል ውስጥ በምታውቀው ትህትናው አናገራት።

ከምትፈራው ነገሩ አንዱ ትህትናው ነው። በዛ ልክ ትሁትና ለተማሪዎቹ የተገባ መምህር ባይሆን ኖሮ አታፈቅረውም ወይም ደግሞ አትከተለውም ነበር። ሲበዛ መልካም መምህር ነው..ለተማሪዎቹ የሚሆን ብዙ ነገር አለው በዚህም ወደደችው።

መልሷ ሲርቅበት የሆነ ነገር እያሰበች እንደሆነ ገባው። ምን እንደሆነ ግን አያውቅም። ፊቱ ላይ ናት..ረጅም ጸጉሯ በከሰዓት በኋላው ኅረምሳ ንፋስ እየተሰቃየ። ሊስቅና ሊያለቅስ በቃጣው መንታ ፊት።

‹ምነው ዝም አልሽ? ምን ላግዝሽ እያልኩሽ ነበር...› ደግሞ ጠየቃት

‹እ..አይ..ምንም..

‹ታዲያ ምን ሆነሽ ነው?

‹ዛሬ ያስተማርከን ብዙም አልገባኝም ጊዜ ካለህ በድጋሚ እንድታስረዳኝ ብዬ ነው...› ደስ የሚልና የሚያሳዝን የተማጽኖ ድምጽ ከአፏ ወጣ።

ለምን የእሱ ትምህርት እንደማይገባት አያውቅም። ክፍል ውስጥ ያልገባው አለ ብሎ ሲጠይቅ ገብቶናል ከሚሉት ውስጥ አንዷ ናት። እግሩ ከክፍል ሲወጣ ግን እንዲህ እንደአሁኑ ሌላ ናት። እሱም እንደ እሷ ብዙ ያልገባው ነገር ነበር..

‹ቅድም እኮ ስጠይቃችሁ እንደገባሽ ነግረሽኝ ነበር...› አላት የምትለውን ለመስማት እንደ ጉድ ቸኩሎ።

‹አዎ ብዬ ነበር!

‹ታዲያ አሁን ምን ተፈጠረ? በጥያቄ ፊቷ ላይ ተንቀዋለለ። የሆነ ልትነግረው የፈለገችው ነገር እንዳለ ዓይኖቿ አሳበቁባት። ጥያቄውን ረስቶ በልቡ ውበቷን ማድነቅ ጀመረ። ቆንጆ እንደሆነች ያውቃል። ቆንጆ ብቻ አይደለም የትኛውም ወንድ የሚፈልጋት ዓይነት ሴትም እንደሆነች ይሄንንም ያውቃል። ዓይኖቿ በቆመበት ያባብሉት ጀመር። ወንድ አይደል የሆነ ስሜት ተሰማው...በልቡ እየከጀላት መጣ። ግን የትኛውም ስሜት ለሀገር ከገባው የአደራ ቃል አይበልጥበትም። የትኛውም ስሜት እምነቱን እንዲሸረሽርበት አይሻም። በሙያው ሀገር ሊለውጥ፣ ዜጋ ሊፈጥር ቃል ገብቷል። በተማሪዎቹ የሚወደድ ብቻ ሳይሆን የሚከበርም መምህር ለመሆን ለራሱ ቃል አለው። በቆመበት በተማሪው ላይ ያሳየውን ያልተገባ የስሜት የበላይነት አባረረ።

‹ደሞ....› የሆነ ነገር ልትለው ብላ ዝም አለች። ሃሳቧ ቆመ..ሃሳቧ ብቻ አይደለም ልቧም የቆመ ይመስላታል። ልቧ ብቻ አይደለም መኖር ያቆመችም ይመስላታል። ምን ልትለው ነበር?

‹ደሞ ምን? ከአፏ ላይ ተቀበላት።

ዝም አለችው..አንድ መዐት ዝምታ። በዝምታዋ ውስጥ ግን እሷና እሱ..ነፍሷና ነፍሱ ነበሩ። በዝምታዋ ውስጥ መቼም የማትረሳው ትህትናው..ጥሩነቱ ነበሩ። በዝምታዋ ውስጥ በእሱ ፊት በኩራት የሚያቆማት ድፍረት ብቻ ነው የሌለው። በዝምታዋ ውስጥ ብዙ አሰበች.. መምህሬ ነው.. እንደ ማፈቅረው ብነግረው እሺ ይለኝ ይሆን? አንድ ተማሪ የሚያስተምራትን ለዛውም ለሴቶች ሁሉ አስፈላጊ የሆነን መልካም መምህር ለፍቅር ብትጠይቅ ምንድነው ችግሩ? ልቧ በዝምታዋ ውስጥ ምንም ችግር የለውም ሲል መልስ ሰጣት። ተደፋፈረች። ዓይኗን ወዳለበት ወረወረች...የሆነ ነገር ብላለች መሰለኝ መልሷን እየጠበቀ በሚመስል ሁናቴ አገኘችው። ትዕግስቱ ይገርማታል..እንደ እሱ ሴት የሚያደምጥ ወንድ አይታ አታውቅም። ሴትን ልጅ የሚማርክ ብዙ ነገር አለው።

‹ምን እያሰብሽ ነው..? የሆነ ነገር ልትይኝ ነበር..።

በዝምታዋ ውስጥ ድምጹን ሰማችው። ድምጹ ያምራታል። ድምጹ የሰፈራቸውን የተንስኦ ጸሎት ያስታውሳታል። እሱ ሲናገርና አባ ተንስኦ ለጸሎት ሲሉ አንድ ነው። በዝምታ ውስጥ ነፍስ ዘራች.. በድምጹ። ዓይኑ ላይ ዓይኗን ተክላ..በሰላ ሴትነት ወንድነቱን እየመረመረች፣ ነፍሱ ጥግ ደርሳ እየተመለሰች፣ ባልተመለሱ ብዙ ጥያቄዎች በዚህ ሁሉ ፊቱ ቆመች።

በሕይወቱ ሴት አጠገብ ቆሞ ምን መናገር እንዳለበት ጥበብ የከዳው ያኔ ይመስለዋል። ምን ያክል እርግጠኛ እንደሆነ ሳያውቅ ጥያቄዋን ተቀብሎ ሊያስረዳት ወደ ቢሮ ጋበዛት።

በላመ ቀይ ፊት፣ የእሳት አሎሎ በሚመስሉ ብርሃናማ ዓይኖች ተከተለችው። የእሱን ባታውቅም እሷ ግን ዓለም ላይ ደስተኛዋን ሴት ሆና ነበር። ቢሮ ሲደርሱ የልቧ ድለቃ ይሰማት ነበር።

በዝምታ ወንበር ስቦ ተቀመጠ። በዝምታ አጠገቡ ወዳለው ወንበር አመላከታት። የዛሬውን የትምህርት ርዕስ የያዘውን መጽሐፍ ጠረጴዛው ላይ ዘረጋው...

አጠገቡ ናት..ነክታው። የሆነ እንግዳ ስሜት ከእሱ ወደ እሷ ሲሰርግ ይሰማታል።

‹የቱ ነው ያልገባሽ? ከእንግዳ ዓለሟ መለሳት።

‹እ...የሚያቃስት ዓይነት ድምጽ ከአንደበቷ ወጣ።

‹ይሄ አልገባኝም..› ጣቷን ወደ መጽሐፉ ጠቁማ እያሳየችው።

‹ይሄን እኮ ቅድም ጥሩ አድርጌ አስረድቻችሁ ነበር..

‹እኔ ግን አልገባኝም..።

እጇ ከመጽሐፉ ላይ ተንሸራቶ እጁን ነካው.. በደንብ ያዘችው።

እያደረገች ያለው ነገር ስላልገባው ዝም አለ።

‹ትቸው..አንተ ውስጥ እንደ ሰለሞን ዓይነት ኃያል ጥበብ ይታየኛል።

‹ምን ዓይነት ጥበብ?

‹እንዲህ እንደ አሁኑ ዓይነት ጥበብ። ከአንተ ወደ እኔ..ከእኔ ወደ አንተ የሚፈስ የሆነ ዓይነት ጥበብ።

ዝም አላት..እንደ ዛሬ ምንም ነገር ገብቶት አያውቅም።

እጆቿን በዝግታ እያንቀሳቀሰች ዳሰሰችው... ሳያውቀው ከሰማያት ሰማያት ቀላቀለችው። እጆቿ አይታክቱም..እጆቿ ነፍስ አላቸው። ጣቶቿ መለኮታዊ ኃይል ተቀብተው አገኛቸው።

ዓይኗን ወደ ዓይኑ ሽቅብ ወረወረች..የሆነ ነገር ልትነግረው መሰለው..ነገረችው

‹አፍቅሬሃለሁ...በአንተ መከራዬን እያየሁ ነው› እንዲህ አለችው።

እንደዛሬ ደንግጦ አያውቅም። ማድረግ ያለበትን በደንብ ያውቃል። ትውልድ ሊቀርጽ ቃል ያለው መምህር ነው።

‹በጣም አዝናለሁ ሳራ..እኔ መምህርሽ ነኝ። አንቺን አስተምሬ ለሀገርሽና ለቤተሰብሽ እንድትበቂ እንጂ ባልተገባ መንገድ ከዓላማሽ ላሰናክልሽ መምህር አልሆንኩም። አንቺ ገና ልጅ ነሽ ወደ ፊት ብዙ ተስፋ ይጠብቅሻል..ትክክል ባልሆነ ነገር ህልምሽን ማጣት የለብሽም። ጥሩና ጎበዝ ተማሪ እንድሆኚ ላግዝሽ ዝግጁ ነኝ።

ቀና ብላ አየችው..ከፍቅሩ በላይ መልካምነቱ ገዛት..ፍቅሩን በመልካምነቱ ቀይራ እንዳላት መምህርና ተማሪ ሆነው ለመኖር ለራሷ ቃል ገባች።

# ዓለም አቀፍ



## ለኮፕ28 ስብሰባ የዓለም መሪዎች ወደ ዐረብ ኢምሬትስ እያመሩ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

ለኮፕ28 ስብሰባ የዓለም መሪዎች ወደ ዐረብ ኢምሬትስ እያመሩ ነው። በፕሬዚዳንት ሼህ መሐመድ ቢን ዛይድ አልነህያን የቀረበላቸውን ጥሪ ተከትሎ በኮፕ28 የአየር ንብረት ለውጥ ስብሰባ ለመሳተፍ የዓለም መሪዎች እና ተወካዮቻቸው ወደ ዐረብ ኢምሬትስ እያመሩ ይገኛሉ።

የቶጎ ፕሬዚዳንት ዶክተር መሐመድ ፋኡሬ ጊናስንግቤ፣ የጉያና ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ዶክተር መሐመድ ኢርፋን አሊ እና የኮትዲቭዋር ፕሬዚዳንት አላሳኔ ኦታራ ከትናንት በስቲያ ዐረብ ኢምሬትስ ገብተዋል።

በተጨማሪም የጊኒ ቢሳው ፕሬዚዳንት ጀኔራል ኦማር ሲሶኮ ኢምባሎ፣ የጋቦን የሽግግር ፕሬዚዳንት ጀኔራል ንጉይማ እና የፓኪስታን የሽግግር ጠቅላይ ሚኒስትር አኑዋር ሀቅ ካካርም ዐረብ ኢምሬትስ ደርሰዋል።

በዱባይ ከኖቬምበር 30 እስከ ዲሴምበር 2 ለሚካሄደው የአየር ንብረት ጉባኤ መሪዎች መምጣታቸውን ቀጥለዋል። ዐረብ ኢምሬትስ ኮፕ 28 በአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይ የተቀመጡ ግቦችን በማሳካት በዓለም ስኬታማ የሆነ ስብሰባ ይሆናል የሚል ተስፋ አላት።

በስብሰባው ሀገራት በአየር ንብረት ለውጥ ዙሪያ የሠሯቸውን ሥራዎች ሪፖርት ያቀርባሉ። ከፓሪሱ የአየር ንብረት ለውጥ ስብሰባ ቀጥሎ በሚካሄደው በዚህ ትልቅ ስብሰባ ከሀገራት መሪዎች በተጨማሪ ዓለም አቀፍ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ወኪሎች በመገኘት መግለጫ ይሰጣሉ ተብሎ ይጠበቃል።

## ኤችአይቪን የሚከላከለው መድኃኒት ውጤታማ መሆኑ በጥናት ተረጋገጠ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ዌልስ ውስጥ በሙከራ ላይ የነበረውና በሰውነት ውስጥ የኤችኤይቪ ቫይረስ ሥርጭትን የሚገታው መድኃኒት ውጤታማ መሆኑ በጥናት ተረጋገጠ። የመድኃኒቱ ውጤታማነት የተረጋገጠው በመላው እንግሊዝ ከተውጣጡ እና በጥናቱ በተካተቱ ከ24 ሺህ በላይ የመድኃኒቱ ተጠቃሚዎች ላይ ምርመራ ከተካሄደ በኋላ ነው።

በእንግሊዝ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ፒአርኢፒ የተሰኘውን ይህን መድኃኒት ከሥነ ተዋልዶ ጤና ክሊኒኮች እየወሰዱ ይገኛሉ። ከቼልሲ እና ዌስትሚኒስትር ሆስፒታል ጋር በመሆን የመድኃኒቱን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የተደረገውን ሙከራ የመራው የዩናይትድ ኪንግደም (ዩኬ) የጤና ደኅንነት ኤጀንሲ፣ ጥናቱ በዓይነቱ ከዚህ ቀደም ከተሠሩ ጥናቶች ሰፊ መሆኑን ገልጿል።

ጥናቱ ከአውሮፓውያኑ ጥቅምት 2017 እስከ ሐምሌ 2020 ባሉት ጊዜያት እንግሊዝ ውስጥ በሚገኙ 157 የሥነ ተዋልዶ ጤና ተቋማት ላይ ተካሂዷል። ይህ ጥናት 'ፕሪ ኤክስፖዠር ፕሮፍላክሲስ (ፒአርኢፒ)' የተባለው መድኃኒት ጥቅም ላይ እንዲውል ማረጋገጫ የሰጠ ሲሆን መድኃኒቱ በኤችአይቪ የመያዝ ዕድልን በ86 በመቶ ይቀንሳል።

በክሊኒክ የተደረጉ ሙከራዎች እንዳመለከቱትም መድኃኒቱ 99 በመቶ ውጤታማ ነው። የዩኬ ጤና ደኅንነት ኤጀንሲ የመድኃኒቱ ውጤታማ መሆን የሀገሪቷ መንግሥት በ2030 የኤችአይቪ ሥርጭትን ዜሮ ለማድረስ ያስቀመጠውን ግብ ለማሳካት ይረዳል ብሏል።

በጥናቱ ላይ የተሳተፉት የሥነ ተዋልዶ ጤና እና ኤችአይቪ አማካሪ ጆን ሳንደርስ እንዳሉት ሙከራው መድኃኒቱ ኤችአይቪን ለመከላከል ውጤታማ መሆኑን ይበልጥ ያሳየ ነው።

ይህም ቀደም ብለው ከተሠሩ ጥናቶች በበለጠ መድኃኒቱ በሽታውን የመከላከል አቅሙን ለመጀመሪያ ጊዜ አሳይቷል ብለዋል። ትሬንስ ሂጊንስ ኤችአይቪ የተባለው ግብረሰናይ ድርጅትም ጥናቱ መውጣቱን በበጎ ተቀብሎ፣ ነገር ግን ተደራሽነትን ለማስፋት፣ ስለመድኃኒቱ ግንዛቤ ለመስጠት ብዙ ሊሠራ እንደሚገባ ጠቁሟል።

የድርጅቱ የፖሊሲ ጉዳዮች ኃላፊ ደቢ ላይኮክ መድኃኒቱ




በመድኃኒት ቤቶች እና በበይነ መረብ (ኦንላይን) ተደራሽ እንዲሆንም ጠይቀዋል። ዶ/ር ሳንደርሰን እንዳሉት ምንም እንኳ ምርምሩ የመድኃኒቱን ውጤታማነት ከማረጋገጡ ባሻገር ጥናቱ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል የሚያስረዱ ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን ይፋ አድርጓል።

«መጀመሪያ ምን ያህል ሰዎች መድኃኒቱን እንደሚፈልጉ እንዲሁም ለምን ያህል ጊዜ መድኃኒቱን ሲወስዱ እንደቆዩ አናውቅም ነበር። አሁን ላይ ግን መድኃኒቱ ለማን መታዘዝ እንዳለበት ተረድተናል። በመሆኑም ብዙ ሰዎችን ለመድረስ ከክሊኒኮች ጋር መሥራት እንችላለን» ብለዋል ሳንደርሰን።

ፒአርኢፒ ቀደም ብሎ የነበሩትን ቴኖፎቪር ዲሶፕሮክሲል እና ኢምትሪሳይታቢን የተባሉ የኤችአይቪ መድኃኒቶችን የያዘ ሲሆን፣ የኤችአይቪ ቫይረስ ወደ ሰውነት እንዳይገባ እና በሰውነት ውስጥ ከገባም በኋላ ራሱን እንዳያባዛ ያደርጋል።

መድኃኒቱ በክኒን መልክ በቀን አንዴ መወሰድ አሊያም ከወሲብ ግንኙነት ቀደም ብሎ መወሰድ ይችላል። ይህንን መድኃኒት እንደ አውሮፓውያኑ በ2020 በእንግሊዝ በስፋት እንዲሰራጭ የተደረገው ቀደም ብሎ በተሠሩ ጥናቶች ውጤት ላይ በመመሥረት ነበር።

አሁን ላይ የጥናቱ ውጤት በላንሴት ኤችአይቪ ላይ የታተመው ሰፋ ያለ ናሙና ስለተወሰደ እና ጥናቱን ሌሎች ተመራማሪዎች ሰፊ ጊዜ ሰጥተው ስለተመለከቱት ነው ተብሏል።

# ስፖርት






## ቀነኒሳ በቀለ በቫሌንሲያ ማራቶን ፈጣን ሰዓት ለማስመዝገብ ይሮጣል

**ብርሃን ፈይሳ**

በዓለም አትሌቲክስ የፕላቲኒየም ደረጃ ከተሰጣቸው የማራቶን ውድድሮች መካከል የፈረንጆቹ ዓመት የመጨረሻ ውድድር የሆነው የቫሌንሲያ ማራቶን ከነገ በስቲያ ይካሄዳል። በስፔን ከሚካሄዱ የጎዳና ሩጫዎች በግዝፈቱ ቀዳሚ በሆነው በዚህ ውድድር ላይ ታዋቂ አትሌቶችን ጨምሮ 30ሺ ሰዎች ይሳተፋሉ። በሁለቱም ጾታዎች በውድድሩ ተሳታፊ መሆናቸው ያረጋገጡ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶችም ፉክክሩን ይበልጥ አጓጊ አድርገውታል።

በተለይ በወንዶች መካከል በሚካሄደው ውድድር በማራቶን ዓለምን ካስደመሙ አትሌቶች ሶስተኛውን ፈጣን ሰዓት ያስመዘገበው ጀግናው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ በቀዳሚነት ትኩረት አግኝቷል። በረጅም ርቀት የመም፣ በሀገር አቋራጭ እንዲሁም በማራቶን ውድድሮች ተደራራቢ ስኬቶችን ማጣጣም የቻለው አንጋፋው አትሌት የሰው ልጅ 42 ኪሎ ሜትርን ከ2ሰዓት በታች መሮጥ ይችላል የሚለውን ሳይንሳዊ እሳቤ እውን ያደርጋሉ ተብሎ ተስፋ ከተደረገባቸው አትሌት አንዱ ነው። የኦሊምፒክና የዓለም ቻምፒዮና የበርካታ ድሎች ባለቤት የሆነው ቀነኒሳ በተደጋጋሚ በሚገጥመው ጉዳት ምክንያት ሙሉ ብቃቱን ማሳየት ባይችልም ይህ ውድድር ግን አዲስ ነገር ሊያሳይበት እንደሚችል ብዙዎች ገምተዋል።

በዓለም አትሌቲክስ ታሪክ ከታዩ እጅግ ድንቅ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች መካከል ቀዳሚ የሆነው ቀነኒሳ፤ በሁለት ኦሊምፒኮች እንዲሁም በአራት



ጀግናው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ በቫሌንሲያ ማራቶን ለአሸናፊነት ይጠበቃል፤

የዓለም ቻምፒዮና መድረኮች በ5ሺ እና 10ሺ ሜትር ርቀቶች 8 የወርቅ፣ 1የብር እና 1 የነሃስ በጥቅሉ 10 ሜዳሊያዎችን ማጥለቅ ችሏል። በሀገር አቋራጭ ውድድርም የእሱን ያህል በድል የተንቆጠቆጠ አትሌት የለም። ወደ ማራቶን ከተሸጋገረም በኋላ በለንደን እና በርሊን ማራቶኖች ተደጋጋሚ ፉክክር በማድረግ በርቀቱ ክብረወሰኑን ለማሻሻል ከጫፍ ደርሶ እንደነበር አይዘነጋም። እአአ በ2019 የበርሊን ማራቶን ያስመዘገበው 2:01:41 የሆነ ሰዓት በወቅቱ የዓለም ክብረወሰን ባለቤት ከነበረው ኬንያዊው አትሌት ኢሉድ ኪፕቾጌ በ2 ሰከንዶች ብቻ የዘገየ ነበር። በቅርቡ የርቀቱ አዲስ ፈጣን ሰዓት መመዝገቡን ተከትሎም የቀነኒሳ ሰዓት ሶስተኛው ሊሆን ችሏል።

በመሆኑም ከቆይታ በኋላ በድጋሚ በሚታይበት በእሁዱ የቫሌንሲያ ማራቶን ፈጣን ሰዓት ወይም ለታሪስ 2024 ኦሊምፒክ ኢትዮጵያን መወከል የሚያስችለውን ውጤት ለማስመዝገብ ተዘጋጅቷል። ቀነኒሳ ለረጅም ዓመት ሲሰለጥን ከቆየበት የማኔጅመንት ቡድን ተለይቶ የቻይናውን ‹‹ANTA›› ከተቀላቀለ የመጀመሪያው ውድድሩ ነው። በመሆኑም በማሸነፍ ታሪኩ የሚታወቀው አትሌቱ በውድድሩ ከባድ ፉክክር ቢገጥመውም ውጤታማነቱን ያስቀጥላል የሚለው የስፖርት ቤተሰቡ ግምት ነው። አትሌቱም በይፋዊ ማህበራዊ ድረ ገጹ ‹‹ከጉዳት በኋላ ብቃቴን ለመፈተን የምሳተፍበት ውድድር እንደመሆኑ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ እንደመሆኔ ውጤታማ ለመሆን ተዘጋጅቻለሁ›› በማለት አስተያየቱን አስፍሯል።

ቀነኒሳ በውድድሩ ላይ ጠንካራ ፉክክር ይገጥመዋል ተብሎ ይጠበቃል። ለዚህም በርካታ የሀገሩ ልጆች እና የጎረቤት ሀገራት ጠንካራ ተቀናቃኝ አትሌቶች በውድድሩ መሳተፋቸው አንዱ ምክንያት ነው። በቡዳፔስት የዓለም ቻምፒዮና በማራቶን የነሃስ ሜዳሊያ ያስመዘገበው አትሌት ልዑል ገብረሥላሴ እና የዘንድሮው ቶኪዮ ማራቶን አሸናፊው ጫሉ ዴሶም ለአሸናፊነት ከሚጠበቁ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች መካከል ይገኛሉ። የታንዛኒያ እና ኬንያ አትሌቶችን ጨምሮም ከ2ሰዓት ከ5ደቂቃ በታች ፈጣን ሰዓት ያላቸውም ናቸው። በሌላ በኩል በ10ሺ ሜትር ወንዶች ከቀነኒሳ ቀጥሎ አስደናቂ ጉዞ በማድረግ ላይ የሚገኘው የ5ሺ እና 10ሺ ሜትር የዓለም ክብረወሰን ባለቤቱ ኡጋንዳዊ አትሌት ጆሽዋ ቺፕቴጌ በቫሌንሲያ ማራቶንን ለመጀመሪያ ጊዜ ይሮጣል። በዶሃ፣ ዩጂን እና ቡዳፔስት የዓለም ቻምፒዮናዎች የበላይነትን ያስመዘገበው ጠንካራው አትሌት ቺፕቴጊ በጎዳና ላይ ሩጫም ስኬታማ የመሆን ተስፋውን የሚለካበት ውድድር እንደሚሆን ይጠበቃል።

እንደወንዶቹ ሁሉ በሴቶች ውድድርም ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች የማሸነፍ ግምት ያገኙ ሲሆን፤ በተለይም አትሌት አልማዝ አያና የአሸናፊነት ቅድመ ግምቱን ልትቀዳጅ ችላለች። በሪዮ ኦሊምፒክ የ10ሺ ሜትር አስደማሚ ድሏ የምትታወሰው አልማዝ እአአ ከ2022 ወዲህ ማራቶንን ተቀላቅላለች። በአምስተርዳም ማራቶን አሸናፊ በመሆን ስኬትን ያጣጣመችው አልማዝ 2:17:20 የሆነ ፈጣን ሰዓት ባለቤትም ናት። ሌላኛዋ ባለፈጣን ሰዓት ኢትዮጵያዊት አትሌት ፀሐይ ገመቹም ለአሸናፊነት ፉክክር የምታደርግ አትሌት ናት። በቡዳፔስቱ የዓለም ቻምፒዮና በአስደናቂ የቡድን ሥራ የተመሰገነችው አትሌቷ የቶኪዮ ማራቶን ተሳትፎዋን በሁለተኛነት ነበር ያጠናቀቀችው። በወቅቱ የገባችበት 2:16:56 የሆነ ሰዓትም የግሏ ፈጣን ሆኖ ተመዝግቦላታል። ወርቅነሽ ደገፋ እና ሕይወት ገብረኪዳንም በውድድሩ የሚሳተፉ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ናቸው።


## ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ

በደ/ኢት/ያ/ክ አሪ ዞን ፋ/ል/መምሪያ በ2016 ዓ.ም ለአስተዳደር እና ቤት እና በስሩ ላለ መምሪያዎች የታሸገ ውሃ የመኪና መለዋወጫ፣ የሞተር ሳይክል፣ የተለያዩ በአሪ ባሕል ልብስ ቀለም የሚሰሩ አልባሳት የመድረክ ዲኮር፣ የቅስቀሳና ፕሮሞሽ ሥራ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች የድምጽ ማጉያ መሣሪዎች የሻይ ቡና እና የተፈቀዱ መስተንግዶ አገልግሎት አቅርቦት እና የሕንፃ መሳሪያ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ተጫራቾችን በማወዳደር በሀገር አተፍ ደረጃ በግልጽ ጨረታ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም ጨረታውን ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች ከታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በማሟላት መወዳደር ይችላሉ፡፡

1. በሁሉም መስኮች ሕጋዊ የንግድ ፍቃድ ያላቸውና ያሳደሱ እንዲሁም የዘመኑን ግብር የከፈሉ፣
2.የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር (tin number) እና ተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ወረቀት ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
3. የንግድ የምዝገባ ሰርተፊኬት እና የአቅራቢነት ምዝገባ ሰርቴፊኬት ያላቸው
4. ተጫራቾች በአሸነፉበት ሎት በራሳቸው ትራንስፖርት እያንዳንዱን ማቅረብ የሚችሉ፡፡
5. የጨረታ ማስከበሪያ የታሸገ ውሃ 25,000.00 ሃያ አምስት ሺህ ብር የመኪና መለዋወጫ 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር የሞተር ሳይክል 30.000.00 /ሰላሳ ሺህ ብር የተለያዩ በአሪ ባሕል ልብስ ቀለም የሚሰሩ አልባሳት 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር/ የመድረክ ዲኮር 5000 ብር አምስት ሺህ ብር የቅስቀሳና ፕሮሞሽ ሥራ 5,000 ብር አምስት ሺህ ብር የኤሌክትሮኒክስ 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር /የሻይ ቡና እና የተፈቀዱ መስተንግዶ አገልግሎት አቅርቦት 5000 ብር አምስት ሺህ ብር የሕንፃ መሣሪያ 20,000 ብር ሃያ ሺህ /በጥሬ ገንዘብ ወይም በCPO በህግ ከታወቀ ባንክ የተረጋገጠ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
6. ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15(አስራ አምስት) ተከታታይ ቀናት ውስጥ የጨረታ ሰነድ የማይመለስ ብር 200/ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ከአሪ አሪ ዞን ፋ/ል/ መምሪያ ግዥ/ ንብ/አስ/ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 12 ቀርቦ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ ::
7. ጨረታው በ16ኛው አስራ ስድስተኛው የሥራ ቀን ከሆነ ብቻ ካልሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን ከጠዋቱ 4፡00 እስከ 6፡30 ሰነዱን አንድ ኦርጅናል እና ሁለት ኮፒ በአንድ እናት ፖስታ በማሸግ ለጨረታው በተዘጋጀው ሳጥን ገቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
8 ጨረታው በዚያው ቀን 8:30 ሰዓት ባለቤቱ ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ ጨረታው ሲከፈት የተጫራቾች ያለመሟላት የጨረታ ሂደቱን አያስተጓጉልም፡፡

መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለበለጠ መረጃ- ስልክ ቁጥር 0916135977

**በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ የደቡብ ኦሞ ዞን**

**ፋይ/ኢ/ል መምሪያ**

## INVITATION FOR BID

## IFB No. ECWCT/NCB/PG-70/2016

1. The Ethiopian Construction Works Corporation (ECWC) hereby invites registered eligible bidders for supply of Tire with Inner Tube.
2. Interested Potential Bidders are required to present renewed relevant Trade License for the Ethiopian fiscal year, VAT Registration Certificate, Tax Clearance Certificate and Online Supplier list Registration Certificate together with their offer.
3. Bidding document should be prepared in English language.
4. Interested Potential Bidders obtain a complete set of bidding document from the office of Procurement Department against payment of none refundable fee of Birr 400.00 upon presentation of Trade License renewed for the fiscal year.
5. This invitation of bid is open to all interested potential bidders regardless of their nationality and the bid evaluation and award shall be determined in accordance with the provision indicated in bidding document.
6. The deadline for bid Submission shall be on December 19, 2023 at 2:30 P.M.
7. Bid must be accompanied with a Bid Security of an amount of Birr 300,000.00 ETB (Three hundred thousand) in the form of certified (CPO) or Bank guarantee. Bid Bond in the form of insurance bond or in any other form shall not be accepted.
8. Bids must be delivered or deposited in the Tender Box situated at the office of the Procurement Department, before the closing date and time.
9. Bids will be opened on December 19, 2023 at 3:00 P.M. in Ethiopian Construction Works Corporation Procurement Department conference room, in the presence of bidders and/or their representatives who choose to attend.
10. The Ethiopian Construction Works Corporation reserves its rights to reject any or all bids.
11. Bidders may get further information at the following address:

Ethiopian Construction Works Corporation

**Address: Gurd shola behind Athletics Federation Building**

**In front of Andinet International school**

**Telephone No. 0118 72 2947/011 8134527**

**Telegram Channel-ECWC.BID**

**Ethiopian Construction Works Corporation (ECWC)**